የፖሊሲ አጭር መግለጫ

ሚያዝያ 2025


የ14 ዓመቷ ልጃገረድ የቤት ውስጥ ሥራዎችን ስታከናውን፣ ሶማሌ ክልል፣ ኢትዮጵያ © ናታሊ በርትራምስ /ጌጅ 2024

# በኢትዮጵያ አፋር እና ሶማሊ ክልሎች የሴት ልጅ ግርዛትና ያለ ዕድሜ ጋብቻ

## ሂደቶች፣ ስጋቶች እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው የለውጥ መግቢያ ነጥቦች

ተመራማሪዎች: ከፍያለው እንዳለ፣ ኤልሳቤጥ ፕሬስለር-ማርሻል፣ ወርቅነህ ያደቴ፣ ኒኮላ ጆንስ፣ ይታገሱ ገበየሁ፣ አብዱላሂ አብዲሰላም፣ ካሳሁን ጥላሁን፣ ጣሰው ወልደሃና እና ኪያ ገዛኸኝ


## መግቢያ

የኢትዮጵያ መንግስት የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለእድሜ ጋብቻን ለማስቆም በቁርጠኛነት እየሰራ ይገኛል። አገሪቱ ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት ሁለቱንም አሠራሮች የከለከለ ጠንካራ የሕግ ማዕቀፍ ያላት ሲሆን፤ እነዚህን ጎጂ ልማዶች ለማስወገድ የተነደፉ በርካታ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችም አሉ (28toomany and Orchid Project, 2023)። ምንም እንኳን እነዚህ የቁርጠኝነት ተግባራት እና የመንግስትና የልማት አጋሮቹ ቀጣይነት ያላቸው ጥረቶች ቢኖሩም የስራው ግስጋሴ በጣም ያልተመጣጠነ እና የታለመለትን ግብ ለማሳካት በጣም ዝግመት የታየበት ነው። ምንም እንኳን የሁለቱም - የሴት ልጅ ግርዛትና ያለ ዕድሜ ጋብቻ - ስርጭት በአገር አቀፍ ደረጃ እየቀነሰ ቢሆንም፣[1] በሕዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ልጃገረዶች ቁጥር ማደጉን ቀጥሏል (ibid.; UNICEF, 2023)። በተለይ በአፋር እና በሶማሊ አርብቶ አደር ክልሎች ያሉ ልጃገረዶች ከፍተኛ ስጋት ላይ ናቸው። በቅርቡ በተደረገው የኢትዮጵያ የስነ-ህዝብ እና የጤና ዳሰሳ ጥናት መሰረት በሁለቱም ክልሎች ከ15-19 አመት እድሜ

1 በ 2005 እና 2016 መካከል፣ ግርዛት የተፈፀመባቸው ከ15–19 አመት የሆናቸው ልጃገረዶች ድርሻ ከ65% ወደ 52% ወርዷል (Elezaj et al., 2019)። በ2005 እና 2016 መካከል፣ ከ18 ዓመታቸው በፊት ያገቡ ወጣት ሴቶች ድርሻ ከ49% ወደ 40% ቀንሷል (Erulkar, 2022)።

ሲጠቅሱ ይህንን ይጠቀሙ፡ ከፍያለው እንዳለ፣ ኤልሳቤጥ ፕሬስለር-ማርሻል፣ ወርቅነህ ያደቴ፣ ኒኮላ ጆንስ፣ ይታገሱ ገበየሁ፣ አብዱላሂ አብዲሰላም፣ ካሳሁን ጥላሁን፣ ጣሰው ወልደሃና እና ኪያ ገዛኸኝ (2025) ‘የሴት ልጅ ግርዛት እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ በኢትዮጵያ አፋር እና ሶማሌ ክልሎች፡ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች እና ስጋቶች።’ ለንደን፡ ሥርዓተ ጾታ እና ታዳጊነት፡ ዓለም አቀፍ ማስረጃዎች።

## ምስል 1: የምርምር ቦታዎች




ክልል ውስጥ በሚገኙ ልጃገረዶች የሴት ልጅ ግርዛት መጠን ከ90 በመቶ በላይ የደረሰና[2] ባለበት የቀጠለ ሲሆን፣ አብዛኞቹ ልጃገረዶች ኢንፊቡሌሽን (ብልትን ተልትሎ አጥብቦ መስፋት) ለሚባለው ለከፋ የሴት ልጅ ግርዛት አይነት የተጋለጡ ናቸው (Central Statistical Agency of Ethiopia (CSA) and ICF, 2017)። ያለ ዕድሜ ጋብቻ ምጣኔውም በጣም ከፍተኛ ነው። ለምሳሌ፣ ከ20 እስከ 24 ዓመት ዕድሜ ካላቸው ወጣት ሴቶች ውስጥ፣ 67% በአፋር ክልል እና 49% በሶማሊ ክልል ከ18 ዓመት ዕድሜያቸው በፊት አግብተዋል (ibid.; Erulkar, 2022)። በመሰረቱ፣ በአገር አቀፍ ደረጃ መሻሻል ቢታይም፣ በአፋርና በሶማሊ ክልሎች ያለዕድሜ ጋብቻ የበለጠ እየተለመደ መጥቷል (CSA and ICF, 2017; Elezaj et al., 2019; Erulkar, 2022)።

ይህ የፖሊሲ አጭር መግለጫ፣ በአይሪሽ እርዳታ የገንዘብ ድጋፍ ከአፋር ሁለት ዞኖች እና ከሶማሊ ሁለት ዞኖች በ2024 የተሰበሰበውን መረጃ፣ ፣ የልጃገረዶች እና የሴቶች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አቅምን ለማዳበር የተቀየሰ፣ በተለይም የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ አደጋዎችን በተመለከተ ከተው የበርካታ ዓመታት የድብልቅ ዘዴ ጥናት የተወሰደ ነው። እ.ኤ.አ. በ 2022 በተካሄደው የመነሻ ምርምር ላይ በመመስረት ተዘጋጀ ነው ሲሆን፣ (Endale et al., 2022ን ይመልከቱ) ሰፊውን የግኝቶችን ሪፖርት በአጭሩ ያቀርባል (Endale et al.፣ 2025)። መግለጫው መጀመሪያ የምርምር ዘዴያችንን ጠቅለል አድርጎ ካቀረበ በኋላ ዋና ግኝታችን በሆነው በሴት ልጅ ግርዛትና ያለ ዕድሜ ጋብቻ ላይ አስፈላጊ መረጃ ይቀርባል። በመጨረሻም፣ የኢትዮጵያ መንግስት በ2030 የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ለማጥፋት በተያያዘው የዘላቂ

## ሰንጠረዥ 1: መጠናዊ ናሙና

| | | አፋር | ሶማሊ | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| ወጣት ሰዎች | ድምር | 961 | 920 | 1881 |
| | ሴት | 824 | 705 | 1529 |
| | ወንድ | 137 | 215 | 352 |
| አሳዳጊዎች | ድምር | 976 | 936 | 1912 |
| | ሴት | 897 | 833 | 1730 |
| | | 79 | 103 | 182 |

## ሰንጠረዥ 2: አይነታዊ ናሙና

| | አፋር | ሶማሊ | ድምር |
|---|---|---|---|
| ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች | 33 (በከፊል ያገቡ) | 32 (በከፊል ያገቡ) | 65 |
| ወንዶች ልጆችና ወጣት ወንዶች | 32 (በከፊል ያገቡ) | 35 (በከፊል ያገቡ) | 67 |
| እናቶች | 36 | 34 | 70 |
| አባቶች | 16 | 16 | 32 |
| ቁልፍ የመረጃ ሰጪዎች | 58 | 55 | 113 |
| ድምር | 175 | 172 | 347 |

2 በአፋር ክልል ከ15-49 አመት እድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙት ሴቶች 91% ያህሉ የሴት ልጅ ግርዛት ተፈጽሞባቸዋል። ዕድሜያቸው ከ15-19 የሆኑ ጥቂት ልጃገረዶች በናሙና ውስጥ የተካተቱ ሲሆን፣ ከእነዚህ ልጃገረዶች ውስጥ 91% የሚሆኑት የሴት ልጅ ግርዛትን ተፈፅሞባቸዋል። በሶማሌ ክልል ከ15-49 አመት ዕድሜ ውስጥ ከነበሩት ሴቶች 99% የሚሆኑት የሴት ልጅ ግርዛት ተፈፅሞባቸዋል። ዕድሜያቸው ከ15-19 የሆኑ ጥቂት ልጃገረዶች በናሙና ውስጥ መካተታቸውን ተከትሎ፣ 95% የሚሆኑት የሴት ልጅ ግርዛትን ተፈፅሞባቸዋል። ዕድሜያቸው ከ15-19 የሆኑ ልጃገረዶች ክልላዊ አኃዞች ያልተመዘነ የኢትዮጵያ የስን ህዝብና ጤና ዳሰሳ ትናት መረጃ በመጠቀም የራሳቸው የተመራማሪዎቹ ስሌት ናቸው።

ልማት ግብ (SDG) 5 ቁርጠኝነት መሰረት የሚወስደውን እርምጃ በፍጥነት ለማሳካት የሚያስችል የፖሊሲ እና የተግባር ለውጦችን በማመላከት እንደመድማለን፡፡

# ግኝቶች

## የሴት ልጅ ግርዛት

### ክስተት፣ አይነቱ እና የተከሰተበት ዕድሜ

ጥናቱ እንደሚያመለክተው፣ በታዳጊነት ዕድሜ ላይ ከሚገኙት ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች መካከል 99% በአፋር እና 80% በሶማሊ ክልሎች ግርዛት ተፈፅሞባቸዋል (ምስል 2ን ይመልከቱ)፡፡ የምጣኔው ልዩነት ድርጊቱ የተፈጸመበትን የጊዜ ልዩነት ያንፀባርቃል፡፡ ይኸውም፣ በአፋር ክልል ሴቶች ልጆች እንደየሚኖሩበት ወረዳ በጨቅላነታቸው ወይም በህጻንነታቸው (በ 2 ዓመት አማካይ ዕድሜያቸው) ግርዛት ይፈፅማሉ፡፡ በሶማሊ ክልል የሴት ልጅ ግርዛት እድሜ ከጋብቻ እድሜ ጋር እየቀነሰ ቢሆንም፣ ልጃገረዶች በመካከለኛው ልጅነት እና መካከለኛ ታዳጊነት እድሜ (በአማካይ በ9.3 አመት እድሜ) የሴት ልጅ ግርዛት ይፈጸማሉ፡፡ ይህ ማለት ገና ያልተገረዙ ታዳጊ ልጃገረዶች አሁንም ወደፊት ግርዛት ለማካሄድ ጊዜ አላቸው፡፡

በሁለቱም ክልሎች ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛት በተስፋፋ ሁኔታ ይገኛል፡፡ አንዲት በሶማሊ የቀበሌ የሴቶች ጉዳይ ዋና መረጃ ሰጪ እንዲህ ብላለች፡ ‘ሴት ልጅ አትገረዝም ማለት የማይታሰብ ነገር ነው፡፡’ በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች የሴት ልጅ ግርዛት ያካሄዱ 100% ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች፣ ዓይነት 3/ብልትን ተልትሎ አጥብቦ መስፋት/ እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል፡፡ አንዲት የ19 ዓመት የሶማሊ ወጣት ሴት ተሞክሮዋን ስትገልጽ፣ ‘የብልቴን ክፍል ከቆረጡ በኋላ በእሾህ ሰፉት… ቁስሉ ለመዳን ከአንድ ወር በላይ ፈጅቶበታል፡፡’ ብላለች፡፡ በአፋር የምርምር አካባቢዎች አብዛኛዎቹ ልጃገረዶች ገና በልጅነታቸው ግርዛት የሚፈጸምባቸው ሲሆን፣ 80% የሚሆኑት ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች ብልትን ተልትሎ ማጥበብ፣ በተለምዶ የጠባሳ ቲሹ፣ የግርዛት አይነት እንደተፈጸመባቸው ተናግረዋል፡፡ ብልታቸውን ተተልትሎ በማጥበብ ካልተሰፉት የአፋር ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች መካከመካከል፣ ሁሉም ማለት ይቻላል ዓይነት 2/ ኤክሴሽን የግርዛት አይነት እንደተፈጸመባቸው ሪፖርት አድርገዋል፡፡ አንድ የአፋር አባት ልማዳዊ ድርጊቶቹን እንዲህ ሲል ገልጸውታል፡፡

በመጀመሪያ የሴቷን ልጅ ቂንጥር ከሥሩ ያስወግዳሉ፤ ከዚያም በሴት ልጅ ቂንጥር ውስጥ በቀኝ እና በግራ በኩል ያለውን ሥጋ ይቆርጣሉ፡፡ ቂንጥሩን እና መላ ሥጋውን ካስወገዱ በኋላ የተቆረጠውን አካል በደም እንዲጣበቅ ለማድረግ እና የብልት ቀዳዳውን ለመዝጋት ወይም ለማጥበብ የልጅቷን ጭን በገመድ ያስሩታል፡፡

### ከእድሜ ጋር የተያያዙ የሴት ልጅ ግርዛት ልምምድ አዝማሚያዎች

በአሳዳጊዎች ላይ የተደረገው ጥናት፣ በቤተሰብ ውስጥ ስለሚኖሩ ሴቶች ሁሉ የግርዛት ሁኔታ አሳዳጊዎቹን ጠይቋል፡፡ ሶስት ግኝቶች ተለይተዋል፡፡ በመጀመሪያ፣ ከ15-17 አመት የሆናቸው ሁሉም (96%) የሶማሊያ ልጃገረዶች የሴት ልጅ ግርዛት እንደተፈጸመባቸው ሪፖርት ተደርጓል፡፡ ሁለተኛ፣ ምንም እንኳን ግርዛት በአፋር በለጋ የልጅነት ጊዜ ሲተገበር የ ቢሆንም፣ ከ6-8 (86%) እና ከ9-11 ዕድሜ ላይ ያሉ (91%) ልጃገረዶች፣ እድሜያቸው ከ12-17 (97%)፣ ከ6-8(86%) እና 9-11 (91%) ከሆኑት ልጃገረዶች የመገረዝ እድላቸው አነስተኛ ነበር፡፡ ምንም እንኳን እነዚህ ቁጥሮች በጥንቃቄ መተርጎም ያለባቸው ቢሆንም፣[3] በአፋር ክልል የሴት ልጅ ግርዛት መጠን እየቀነሰ ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማሉ፡፡ በሦስተኛ ደረጃ፣ በአፋርም ሆነ በሶማሊ ክልል፣ የዓይነት 3 የግርዛት አይነት ከተፈጸመባቸው መካከል፣ በየዕድሜ ክልሉ ያለው ስርጭት በአብዛኛው የማይለያይ ቢሆንም፣ የልጃገረዶች ብልት ከመዘጋቱ በፊት

ምስል 2፡ በታዳጊ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታ፣ በክልል በክልል




3 ይህ የሆነበት ምክንያት ናሙና በተወሰደባቸው ቤተሰቦች ውስጥ የሚኖሩ ጥቂት ትናንሽ ልጃገረዶች በመኖራቸው ነው (በናሙና አወሳሰድ ምክንያት በታዳጊነት ዕድሜ ላይ ባሉ ወጣቶች ላይ አተኩሯል)፡፡

የብልት አካል ተቆርጦ ሚወገዱበት መጠን ቀስ በቀስ የቀነሰ ይመስላል። በአፋር የምርምር አካባቢዎች፣ ከ9 አመት በላይ የሆናቸው የሴት ልጅ ግርዛት ከተፈፀመባቸው ልጃገረዶች እና ሴቶች ውስጥ ከሶስት አራተኛ በላይ የሚሆኑት ብልት በመስፋት የማጥበብ አይነት ግርዛት እንደተፈጸመባቸው ታውቋል።

ይህ የሆነበት ምክንያት ናሙና በተወሰደባቸው ቤተሰቦች ውስጥ የሚኖሩ ጥቂት ትናንሽ ልጃገረዶች በመኖራቸው ነው (በናሙና አወሳሰድ ምክንያት በታዳጊነት ዕድሜ ላይ ባሉ ወጣቶች ላይ አተኩሯል)።

ዕድሜያቸው ከ8 ዓመት በታች የሆኑ እና የሴት ልጅ ግርዛት ከተፈጸመባቸው ልጃገረዶች መካከል የግርዛት ምጣኔ ከፍ ያለ ነበር። ነገር ግን ከ18 ዓመት በላይ የሆናቸው 56 በመቶው የአፋር ሴቶች እና 48 በመቶው ከ12-17 ዓመት የሆናቸው ልጃገረዶች የሴት ብልት መዘጋት፣ የፊት፣ የውስጥ እና የውጭ የብልት ከንፈር መወገድ የተፈጸመባቸው ቢሆንም፣ ተመሳሳይ ነገር የደረሰባቸው ዕድሜያቸው 8 እና ከዚያ በታች የሚሆኑት የአፋር ልጃገረዶች 35% ብቻ ናቸው። በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች ላይ ተመሳሳይ ለውጦች ይታያሉ። ምንም እንኳን 90% የሚሆኑት በቤተሰብ ውስጥ ግርዛት ከተፈጸመባቸው ሴቶች መካከል 90% የብልት አጥብቦ መሰፋት የተፈጸመባቸው ናቸው ተብሎ ሪፖርት የተደረገ ቢሆንም፣ የእድሜ ክልል ምንም ይሁን ምን፣ የሴት ልጅ ብልት ከመሰፋቱ በፊት የብልታቸው የውስጥና የውጭ ከንፈሮች ተቆርጦ እንዲወገድ የተደረገባቸው በመቶኛ መቀነስ አሳይቷል። ይህም የሆነው 51% ዕድሜያቸው 18 እና ከዚያ በላይ በሆናቸው ጎልማሶች፣ 44% ዕድሜያቸው ከ12–14 አመት በሆናቸው ልጃገረዶች እና 37% ከ6-11 እድሜ ባላቸው ልጃገረዶች ላይ ነው።

አይነታዊ ምርምሩ እንደሚያመለክተው በአፋር የምርምር አካባቢዎች ውስጥ ባሉ የዕድሜ እኩዮች መካከል ያለው የሴት ልጅ ግርዛት መጠን እየቀነሰ መምጣቱ ድርጊቱ ያልተለመደ እየሆነ መጥቷል ብሎ ለመደምደም አያበቃም። ምንም እንኳን ብዙ ምላሽ ሰጪዎች የሴት ልጅ ግርዛት ያልተፈጸመባቸው የትንንሽ ልጃገረዶች ቡድን ቁጥር እያደገ መምጣቱን ቢናገሩም፣ ይህ በዋነኛነት ሴቶች ድርጊቱን በመተዋቸው የቁሳቁስ ስጦታ የተደረገላቸው በመሆኑ ምክንያት ሲሆን እንዲሁም የሴት ልጅ ግርዛት በሚፈፀምበት ጊዜ ከሚደረጉ ለውጦች ጋር የተያያዘ ነው። አንድ የ15 አመት ልጅ ከአፋር እንዲህ ሲል ገልጿል።

*ያልተገረዘች የ7 አመት እህት አለችኝ። ብዙ ያልተገረዙ ጓደኞቿ አሏት…ወደፊት እናደርገዋለን።*

በሁለቱም ክልሎች ያሉ ምላሽ ሰጪዎች የሴት ልጅ ግርዛትን በማስቀጠል ልማዳዊ (የበለጠ የተሰፋፉ) ድርጊቶችን ብቻ ከግምት ውስጥ እንደሚያስገቡ እና እንዲያውም እነዚህን ልማዳዊ ድርጊቶች አለመፈጸም ከተፈቀደው (ሱና) ድርጊት ማፈንገጥ እንደሆነ አድርገው የሚቆጥሩት እንዳለ ሆኖ፣ አይነታዊ ምርምሩ በብዛት በከተሞች አካባቢ ቀለል ያሉ የግርዛት አይነቶችን የሚፈጽሙ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አግኝቷል። በአፋር የምርምር አካባቢዎች፣ ወጣት ልጃገረዶች የብልታቸው ትንሽ ሥጋ ብቻ እንደሚቆረጥ እና/ወይም ከዚያም በኋላ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ጭኖቻቸው አንድ ላይ እንዲታሰር በመደረጉ ጠባሳው አነስተኛ እንዲሆን እንዳደረገ ምላሽ ሰጪዎች ተናግረዋል። አንድ አባት ከአፋር ስለ ሴት ልጆቹ እንዲህ ብሏል፡

*የመጀመሪያዋ ሴት ልጄ በቀድሞው መንገድ ነው የተገረዘችው፣ ሌሎቹ ሴቶች ልጆቼ አልተገረዙም… የመጀመሪያዋ ልጄ በመገረዟ ብዙ ተሠቃይታለች። ህመሟን ካየሁ በኋላ ሌሎች ሴት ልጆቼን በአዲሱ መንገድ ለማስገረዝ ወሰንኩ።*

በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች፣ ወጣት ልጃገረዶች የብልታቸው ሥጋ ተቆርጦ የተወገደባቸው አነስተኛ መሆኑን እና/ወይም ብልታቸው ከስድስት ወይም ሰባት ጊዜ ይልቅ አንድ ወይም ሁለት ጊዜ ብቻ እንደተሰፋ ምላሽ ሰጪዎች ተናግረዋል። አንዲት የ22 ዓመቷ የሶማሊ ወጣት ሴት የመሰፋት ደረጃው ብቻ እንደሚለያይ ገልጻለች፡ 'ሱና የሚለየው በብልት መሰፋት ብቻ ነው። የብልት መቆረጡ ግን ተመሳሳይ ነው።'

### የሴት ልጅ ግርዛት ህጋዊ ክልከላዎች ግንዛቤ

በበሴት ልጅ ግርዛት ህጋዊ ክልከላዎች ላይ ያለው ግንዛቤ በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች መካከል እና በክልሎቹ ውስጥ በእጅጉ ይለያያል። ጥናቱ እንደሚያመለክተው በአፋር የምርምር አካባቢዎች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች (52%) እና አሳዳጊዎች (61%) በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች ካሉት ወጣቶች (18%) እና አሳዳጊዎች (27%) ይልቅ የሴት ልጅ ግርዛትን የሚከለክል ብሄራዊ ህግ[4] እንዳለ የመገንዘብ እድላቸው ከፍ ያለ ነው። (ምስል 3ን ይመልከቱ)። ይህም ሲባል፣ በአይነታዊ ቃለ-መጠይቆች ወቅት፣ በሁለቱም ክልሎች ያሉ ምላሽ ሰጪዎች የሴት ልጅ ግርዛት ድርጊቶች ላይ ለውጥ የመኖሩ ምክንያት በባህላዊ ግርዛት ፈጻሚዎች እና በወላጆች ላይ የሚደረጉ ቅጣቶች መሆናቸውን ማወቅ መቻላቸው ያልተለመደ አልነበረም። የሶማሊ ክልል ነዋሪ የሆነች የ17 ዓመቷ ወጣት እንደገለፀችው ባሕላዊ ገራዦች እስር ቤት መግባት ስለሚፈሩ ከዚህ በኋላ የልጃገረዶችን ብልት ከአምስት እስከ ሰባት ጊዜ እየሰፉ አይቀጥሉም፡

*ማንም ግርዛት ፈጻሚ የሴት ልጆችን ብልት መስፋት አይፈልግም። ያን ሲያደርጉ ከተገኙ ወደ ወረዳው ከተማ ተወስደው እዚያው ይታሰራሉ።*

ለሌሎች ባህሎች መጋለጥ በብዛት በሚታይባቸው የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች የሴት ልጅ ግርዛትን ለመቀረፍ ፍቃደኛ በሆኑባቸው እና በሥርዓተ-ፆታ ላይ ያተኮሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ረዘም ላለ ጊዜ ሲንቀሳቀሱ በነበሩባቸው በአፋር የምርምር አካባቢዎች የሚገኙ ምላሽ ሰጪዎች እነዚህ ሁሉ ለለውጡ አስተዋፅኦ እንዳደረጉ ተናግረዋል።

4 አፋርም ሆነ ሶማሌ ብሄራዊ ህጉን አላፀደቁትም። በክልል ደረጃ የሴት ልጅ ግርዛት ህጋዊ ሆኖ ቀይቷል።

## የሴት ልጅ ግርዛትን የሚደግፉ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ እምነቶች

አብዛኞቹ ምላሽ ሰጪዎች፣ ምንም እንኳን በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ለውጥን ለማምጣት የህግ እና የጤና መልእክቶች አስፈላጊ ቢሆኑም፣ ገና በመሻሻል ላይ ያለው ተጽዕኖ ፈጣሪው የሃይማኖት መሪዎች ስብከት እንደሆነ በግልጽ ተናግረዋል። የእምነት መሪዎች ዋናው መልእክት የሴት ልጅ ብልት መስፋት መቅረት የሚገባው ቢሆንም ቂንጥርን ማስወገድ ግን በእስልምና ይፈቀዳል ወይም ይፈለጋል የሚል ነው።[5] አንድ አባት ከአፋር፣ "ሃይማኖታችን የሆነው እስልምና ስለ ግርዛት ከሚናገረው ጋር የሚስማማ በመሆኑ ነው አስተምህሮውን የተቀበልነው።" ሲሉ ገልጸዋል።


አንዳንድ ጊዜ መለስተኛ የሴት ልጅ ግርዛት እንደ ግርዛት የሚታይ አለመሆኑ እና እስልምና የአፋርም ሆነ የሶማሊ ባህል ዋና መገለጫ ተደርጎ የሚወሰድ እንደመሆኑ መጠን፣ በሴት ልጅ ግርዛት እና በሃይማኖት መካከል ስላለው ግንኙነት ያሉ አመለካከቶች ውስብስብ እና ለመለየት አስቸጋሪ ናቸው። በአፋር የምርምር አካባቢዎች፣ ለአጎራባች የአማራ ባህል በመጋለጣቸው ምክንያት፣ ቂንጥር መቁረጥ የግርዛት አይነት መሆኑን የመገንዘብ እድላቸው ሰፊ ነው። አብዛኞቹ ወጣቶች (66%) እና ተንከባካቢዎች (76%) የሴት ልጅ ግርዛት በሀይማኖት እንደሚፈለግ ተናግረዋል (ምእል 4ን ይመልከቱ)። አንዲት የ22 ዓመ እናት እንዲህ ብላለች፦

> ሴት ልጄ እንድትገረዝ አልፈልግም ነበር… በጣም መጥፎ ነው። ብትሞት ካልተገረዘች ገነት አትገባም።

እንደተባለው፣ ዋና የሴት ልጅ ግርዛት ምክንያት ምን እንደሆነ የአፋር ምላሽ ሰጪዎች ሲጠየቁ፣ ከሀይማኖት (28%) ይልቅ የባህል ማንነትን (39% ወጣቶች) ሪፖርት የማድረግ እድላቸው ከፍ ያለ ነበር። አንዲት እናት የሴት ልጅ ግርዛት እና ብልት መሰፋት የአፋርን ባህል በዙሪያው ካሉት እንደሚለይ እንዲህ ስትል በኩራት ተናግራለች። "እኛ ተገርዘናል፤ ለዚህም ነው ልጆቻችንን የምናስገርዘው። ከኛ በቀር ይህ ባህል ያለው ማንም የለም።" በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች የሚገኙ ምላሽ ሰጪዎች፣ በተለይ ግርዛት ማለት የብልት መሰፋትን እንደሆነ የሚያስቡ፣ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው አሳዳጊዎች (35%) እና ወጣቶች (41%) የሴት ልጅ ግርዛት ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው ሲሉ ሪፖርት አድርገዋል። ሆኖም ግን የሴት ልጅ ግርዛት ዋና ምክንያት ምን እንደሆነ ሲጠየቁ ሁለቱም ምላሽ ሰጪዎች  ከባህል ይልቅ ሀይማኖትን የመምረጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው (ለምሳሌ ለአሳዳጊዎች፣ 45% ሃይማኖት፤ እና 34% ባህል)። አንድ የትምህርት ባለሙያ ከሶማሊ እንዲህ ሲል ገልጿል።


ሃይማኖትን በሚመለከት፣ አንድ ሰው ከ10 አመቱ ጀምሮ ሶላትን እንዲጀምር የተሰጠ መመሪያ ነው። በሀይማኖቱ መሰረት ቸ በዛ እድሜያቸው መገረዝ አለባቸው። አለበለዚያ የልጃገረዶች ጸሎት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ላይኖረው ይችላል። በማህበረሰቡ ዘንድ ያለው እምነት ይህ ነው።

አንድ የ20 አመት ወጣት እስልምና የሚፈልገው የሴት ልጅ ግርዛትን ብቻ እንጂ በአብዛኛው በገጠር አካባቢዎች በስፋት



ምስል 3፡ የሴት ልጅ ግርዛት ህገወጥ መሆኑን የማወቅ በዕድሜና በክልል

5 እስልምናን እና የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ አራት ዋና ዋና የአስተሳሰብ ትምህርት ቤቶች አሉ። ለዝርዝር መረጃ፣ Islamic Relief Worldwide (2018) One cut too many: Islamic Relief policy brief on female genital mutilation/cutting. ይመልከቱ። በሶማሌ የየክልል የእምነት መሪዎች በ2023 ብልት መስፋትን በጥብቅ የሚቃወም ውሳኔ አውጥተዋል።



ምስል 4: ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ከሃይማኖትና ባህል አንጻር የተሳታፊዎች እምነት፣ በዕድሜና በክልል

የሚታየውና እንደ ባህላዊ መስፈርት የሚቆጠረውን የብልት መሰፋትን እንዳልሆነ አስረድቷል፡፡ ‘ሃይማኖቱ የሚነግረን ስለ ግርዛት ብቻ ነው እንጂ የልጅቷን ብልት ስለ መስፋት አይደለም… ይህ የሆነው በባህል ምክንያት ነው፡፡’ ብሏል፡፡

## ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ጥቅምና ጉዳት ስሌት

ጥናቱ እንደሚያሳየው በሁለቱም ክልሎች ጥናት በተደረገባቸው አካባቢዎች ያሉ ወጣቶች እና አሳዳጊዎች የሴት ልጅ ግርዛት ማህበራዊ ጠቀሜታ እንዳለው ማመን የተለመደ ነበር፡፡ ምጣኔው በሶማሊ ባሉ ወጣቶች ከዝቅተኛው 35% እስከ በአፋር ባሉ አሳዳጊዎች ከፍተኛ 52% ደርሷል (ምስል 5ን ይመልከቱ)፡፡ የተዘገበው የሴት ልጅ ግርዛት ጥቅሞች በየክልሎቹ፣ እና በሶማሊ በጾታ፣ ይለያያሉ፡፡ በአፋር የምርምር አካባቢዎች፣ ከሴት ልጆች እና ወጣት ሴቶች በስተቀር ሌሎች ምላሽ ሰጪዎች የሴት ልጅ ግርዛት ዋነኛ ጥቅም የሴቶችን (እና የሴቶችን) የወሲብ ፍላጎት መቆጣጠር እንደሆነ የሰሙ ቢሆንም ነገር ግን በግላቸው አላመኑበትም፡፡ አንድ አባት እንዲህ ብለዋል:

ልጃገረዶች ካልተገረዙ ከፍተኛ የወሲብ ፍላጎት ይኖራቸዋል፤ እናም ከአንድ ወንድ/ባል ጋር ብቻ አይቆዩም፤ ዝሙት ይፈጽማሉ ወይም ከጋብቻ በፊት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ይጀምራሉ፡፡

በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች፣ ሴት ምላሽ ሰጪዎች ብዙውን ጊዜ የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ ሴቶች ልጆች (እና እናቶች) በማህበረሰብ ውስጥ ስላላቸው ቦታ አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ አንዲት እናት እንዲህ ስትል ገልጻለች:

አለመገረዝ ያሳፍራል፡፡ እኔ ሶማሊ ስለሆንኩ ልጄ መገረዝ አለባት፡፡ ሴት ልጄን ካላስገረዝኩ ሌሎች ደግሞ ሴት ልጇን እንደማታስገርዝ ሴት እየፈረጁ ይሰድቡኛል፡፡ ከዚህም በላይ ልጅቷ ያልተገረዘች ተብላ ትፈረጅና እንድትሸማቀቅ ይሆናል፡፡


ወንዶች ልጆችና ወንዶች በተቃራኒው የሴት ልጅ ግርዛት ለሴት ልጆች ድንግልናቸውን ስለሚያረጋግጥ ለጋብቻ አስፈላጊ እንደሆነ አጽንኦት ሰጥተዋል አንድ የ15 ዓመት ልጅ እንዲህ ሲል ተናግሯል: “ሴት ልጆች ካልተገረዙ አያገቡም፡፡” በሁለቱም ክልሎች የሴት ልጅ ግርዛት ሴት ልጆችን ብልታቸውን በመስፋት ከአስገድዶ መድፈር እንደሚከላከል ይታሰባል፡፡

የሴት ልጅ ግርዛትን ጉዳት በተመለከተ ከፍተኛ የክልላዊ ልዩነቶች ነበሩ፡፡ በአፋር የምርምር አካባቢዎች ያሉ ምላሽ ሰጪዎች በሶማሊ ካሉት በእጥፍ የሚሆኑት (በወጣቶች መካከል በአፋር 73% እና በሶኦማሊ 41%) የሴት ልጅ ግርዛት ጉዳት ያለው መሆኑን ገልጸዋል (ምስል 5ን ይመልከቱ)፡፡ በአፋር ክልል የሚገኙ ምላሽ ሰጪዎች ብዙውን ጊዜ የሴት ልጅ ግርዛት በልጃገረዶች ላይ ከባድ ህመም እንደሚያስከትል፣ የዕድሜ ልክ የሽንት እና የማህፀን በሽታዎችን እንደሚያስከትል፣ በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወቅት ህመም ሊያስከትል እንደሚችል ገልጸዋል፡፡ በአንፃሩ፣ በሶማሊ ያሉ እኩዮቻቸው ድርጊቱ ምንም አይነት አደጋ እንደሌለው ያምናሉ፡፡

የ21 ዓመቷ የሶማሊ ወጣት ሴት በብልት መሰፋት ምክንያት የጤና ችግር ገጥሟት እንደሆነ ስትጠየቅ፣ “ምንም የለም… ለኛ ጥሩ ነበር፡፡” ብላለች፡፡ የሶማሊ ወጣቶች በተለይ የሴት ልጅ ግርዛትን ስጋት ይዘነጉት ነበር፡፡ በልጁ በቀዶ ህክምና መወለድ የተሰማውን ጭንቀት የገለፀው የ21 አመቱ የሶማሊ ወጣት ከግርዛት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለው ተናግሯል፡፡

ልጄ በቀዶ ሕክምና ተወለደ፡፡ በዚያን ጊዜ በጣም ተጨንቄ ነበር… እህቴ ሰባት ልጆችን ወልዳለች፡፡


ምስል 5፡ የሴት ልጅ ግርዛት ጥቅሞችና ጉዳቶች፣ በዕድሜና በክልል




## በሁሉም ሁኔታዎች ለቀዶ ህክምና ሄዳለች። ለቀዶ ህክምና መሄድ የተለመደ ነው።

የሚገርመው፣ የሴት ልጅ ግርዛትን ጉዳት በተመለከተ ከክልላዊ ልዩነቶች አንጻር፣ የድርጊቱን ድንገተኛ ሕክምና ማስረጃ ያገኘነው በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች ብቻ ነው። ምንም እንኳን ጥናቱ እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ የሶማሊ ልጃገረዶች ልክ እንደ አፋር እኩዮቻቸው በባህላዊ ገራዦች ግርዛት የሚፈጸምባቸው ቢሆንም፣ አንዳንድ የሶማሊ የአይነታዊ ምርምር ተሳታፊዎች ሴት ልጆች በጤና ባለሙያዎች እየተገረዙ እንደሚገኙ ጠቁመዋል ይህም አይነት 1 ግርዛት/ የቂንጥር መቁረጥ ሲሆን በባህላዊ ገራዦች የአይነት 3 ግርዛት /መሰፋት እንዳይደርስባቸው ለመከላከል ነው። ሌሎች የሶማሊ ምላሽ ሰጪዎች እንደገለፁት

ምስል 6፡ ስለ ወደፊት ሚስቶቻቸው ግርዛት አይነት የወንዶች ልጆችና ወጣት ወንዶች ምርጫ፣ በክልል



ባህላዊ ገራዥች በአሁኑ ጊዜ ሴት ልጆች ግርዛት ሲያደርጉ እና በሚያገቡበት ጊዜ የግብረ ስጋ ግንኙነት ይጀምራሉ ተብሎ በሚጠበቀው ሰዓታት ውስጥ የተሰፋው በቢላዋ መቀደድ ስለሚኖርበት የህመም ማስታገሻ እና መዳህኒቶችን ይሰጧቸዋል።

### ወጣት ወንዶች ለሴት ልጅ ግርዛት ያላቸው ድጋፍ

የሴት ልጅ ግርዛት ከባህላዊ የወንድነት አስተሳሰብ ጋር ውስብስብ ትስስር አለው። በአፋር (72%) እና በሶማሊ (85%) የምርምር አካባቢዎች አብዛኞቹ ወንዶች እና ወጣቶች የሴት ልጅ ግርዛት የተፈፀመባትን ሚስት ማግባት እንደሚመርጡ ተናግረዋል (ምስል 6ን ይመልከቱ)። በአፋር ውስጥ፣ የወጣት ወንዶች ዋነኛ ምርጫ ዓይነት 1/ ቂንጥር መቁረጥ አይነት ግርዛት የተደረገላት ሚስት ማግባት ባየለበት ሁኔታ፣ የሴት ልጅ ግርዛት አይነት ምርጫዎች ስለ ግርዛት ጥቅሞች ከሚደግፉ እምነቶች ጋር የተጣጣሙ ናቸው። ይኸውም ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል ስለልጃገረዶች (እና የሴቶች) ከፍተኛ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ፍላጎት ጋር በተያያዙ እምነቶች የተነሳ ነበር። የ22 ዓመቱ ወጣት እንዲህ ሲል ገልጿል።

በአሁኑ ጊዜ በአካባቢያችን ያሉ ወንዶች/ወንዶች ልጆች ቀደም ሲል የነበረውን የሴት ልጅ ግርዛት የሚያስከትለውን ውጤት ጠንቀቀው ስለሚያውቁ ቂንጥር የተቆረጠባቸውን ልጃገረዶች ያገባሉ። ያልተገረዘችን ሴት ግን ማንም ሊያገባት አይችልም። ምክንያቱም የልጃገረዶች ቂንጥር መቁረጥ ልጃገረዶች የወሲብ ፍላጎታቸውን እንዲቀንሱ ይጠቅማቸዋል።


በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች፣ 31% የሚሆኑ ወጣት ወንዶች ዓይነት 3/የብልት መሰፋት ግርዛት የተደረገላትን ሚስት እንደሚመርጡ ሪፖርት ሲያደርጉ፣ ምርጫቸው አሁንም የሴት ልጅ ግርዛት ጥቅሞች ከልጃገረዶች ከጋብቻ በፊት የግብረስጋ ግንኙነት ከማድረግ ስጋቶች ጋር ከተያያዙ እምነቶች ጋር የተጣጣሙ ነበሩ። አንድ የ19 ዓመት ወጣት እንዲህ ሲል ገልጿል። “ካልተሰፉች እንደ ፈታች ትቆጠራለች። … ወንዶች ድንግል የሆነች ሴት ይፈልጋሉ።” ሌላው በተመሳሳይ ዕድሜ ያለ የሶማሊ ወጣት አክሎም እሱና እኩዮቹ የተሰፋች ሚስት ማግባት ቢመርጡም፣ የተሰፋውን የልጅቷን ብልት ለመክፈት ከነሱ ይልቅ የእናቶቻቸው ጥረት እንደሚበልጥ ገልጿል። “ወንዶች የተሰፋውን የልጃገረዶች ብልት መክፈት አይፈልጉም፤ ይልቁንም ቁጥር አንድ አጋዥ የሆኑት እናቶች ናቸው።”


ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ቀጣይነት ያለው አመለካከት

በተለይ በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች፣ ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ጉዳት ያላቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ በሚመስልበት ሁኔታ፣ ስለ ሀይማኖት፣ ባህል እና የሴት ልጅ ጾታዊ ግንኙነት ያላቸው እምነት የተቀራኘ መሆኑ እንደተጠበቀ ፣ የሴት ልጅ ግርዛት እንዲቀጥል የሚደረገው ድጋፍ ከፍተኛ ነው። በአፋር ክልል ጥናቱ ከተካሄደባቸው ወጣቶች መካከል 30% ወጣቶች እና 38% አሳዳጊዎች የሴት ልጅ ግርዛት መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል (ምስል 7ን ይመልከቱ)።

በሶማሊ የተገኙት ተመሳሳይ አሃዞች 54% እና 55% ነበሩ። የሚገርመው ነገር፣ የወደፊት ሴት ልጆቻቸውን ለማስገረዝ ያስቡ እንደሆነ ሲጠየቁ፣ የወጣቶች ምላሽ ድርጊቱን እንዲቀጥል ካላቸው ፍላጎት ጋር አልተጣጣመም። በአፋር የምርምር አካባቢዎች፣ ወጣቶች ለሴት ልጅ ግርዛት ቀጣይነት ካላቸው ድጋፍ (40%) ይልቅ በራሳቸው ሴት ልጆች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ያላቸው ፍላጎት (30%) ከፍተኛ ነበር። በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች፣ በተቃራኒው ወጣቶች ለሴት ልጅ ግርዛት ቀጣይነት ካላቸው ድጋፍ (54%) ይልቅ

ምስል 7፡ ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ቀጣይነት ድጋፍ፣ በዕድሜና በክልል





ምስል 8፡ በወደፊት ሴት ልጆቻቸው ላይ ግርዛት የማካሄድ ፍላጎት፣ በክልል

በራሳቸው ሴት ልጆች ላይ ተግባራዊ ለማድረግ ያላቸው ፍላጎት (46%) አነስተኛ ነበር፡፡ የወንዶች ልጆች እና ወጣት ወንዶች ለወደፊት ሚስታቸው ያላቸው የግርዛት ምርጫ ላይ እንደታየው ሁሉ፣ በአፋር ክልል ውስጥ ያሉ የዳሰሳ ጥናቱ ታሳታፊ 92% ወጣቶች በወደፊት ሴት ልጆቻቸው ላይ ዓይነት 1/የቂንጥር መቁረጥ የግርዛት አይነትን ተግባራዊ ለማድረግ ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡ በሶማሊ ክልል ያሉ አብዛኞቹ ወጣቶች ዓይነት 2/ኤክሴሽን (39%) ወይም ዓይነት 3/የብልት መስፋትን (20%) የመምረጥ ፍላጎት እንዳላቸው ተናግረዋል፡፡

### ስለ ሴት ልጆቻቸቸው ግርዛት የአሳዳጊዎች እምነቶች እና ውሳኔዎች

የሴት ልጅ ብልት መስፋትን፣ ባጠቃላይ ግርዛትን ለማስወገድ የሚነደፍ ፕሮግራም እናቶች እና አባቶች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት ያላቸውን እምነት ክልላዊ ልዩነት ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡ በአፋርም ሆነ በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች፣ እናቶች - የራሳቸው ማህበራዊ ደረጃ ከግርዛት ተግብራቸው ጋር የተቆራኘ እና የሴት ልጅ ግርዛትን ካቋረጡ ያልተገረዙ ሴት ልጆቻቸው ከማህበራዊ ኑሮ እንደሚገለሉ ጠንቅቀው የሚያውቁ እናቶች - ግርዛት ጠቃሚና የሀይማኖት ግዴታ ነው በማለት ከአባቶች በ10 በመቶ ብልጫ አሳይተዋል (ምስል 9ን ይመልከቱ)፡፡ በአፋር ክልል በርካታ አባቶች ትልልቅ ሴት ልጆቻቸው በመገረዛቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን ስቃይ ካዩ በኋላ ለታናናሽ ሴት ልጆች መለስተኛ ግርዛት እንዲደረግላቸው ሲያደርጉ፣ ግርዛትን ጉዳት ላይ ይጥላል ያሉ እናቶች ቁጥር ከአባቶች በ14 በመቶ ያነሰ ነው (እናቶች 71%፤ አባቶች ከ85 በመቶ በላይ)፡፡

የሴት ልጅ ግርዛት ውሳኔም እንደየክልሉ ይለያያል፡፡ በአፋር የምርምር አካባቢዎች እናቶች እና ሴት አያቶች ሴት ልጆች መቼ እና በማን እንደሚገረዙ የመወሰን ሃላፊነት ሲኖራቸው፣ አባቶች ሴት ልጆቻቸው በሚያደርጉት የግርዛት አይነት ላይ የሚሰጡት ሃሳብ ጥቂት እንደሆነ ምላሽ ሰጪዎች ገልጸዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ስለ ሁሉም የሴት ልጅ ግርዛት ገጽታዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራው ከእናቶች እና የወደፊት እናቶች በተጨማሪ በአባቶች እና በወደፊት አባቶች ላይ ማነጣጠር አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች ያሉ ምላሽ ሰጪዎች ግን  የሴት ልጅ ግርዛት ውሳኔ የእናቶች ስልጣን እንደሆነ እና አባቶች እና አያቶች ከውሳኔ ሰጪነት የተገለሉ መሆናቸውን ተስማምተዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው በዚህ ክልል ውስጥ የሚነደፍ ፕሮግራሚንግ በእናቶች እና የወደፊት እናቶች ላይ ማተኮር እንዳለበት፣ እንዲሁም እናቶች የወንድ ልጆቻቸውን የወደፊት ሚስታቸው የግርዛት ምርጫ እንዴት እንደሚቀርፁ እና እንዴት እንደሚያስቀጥሉ ነው፡፡ አንዲት እናት ከሶማሊ ክልል እንዲህ ስትል ገልጻለች፡፡


በሶማሊ ባህል የሴቶችን ግርዛት በተመለከተ ሴቶች ውሳኔ ሰጪዎች ናቸው… ባሎች ሴቶች እንዲገረዙ ባይፈቅዱም እናቶች እንዲገረዙ ያስገድዷቸዋል… ባሌ ወደ ሌላ ቦታ ሲሄድ ሁለቱን ልጆቼን አስገርዣለሁ፡፡ እሱ እዚህ ቢሆን ኖሮ ድርጊቱን እንዳከናውን አይፈቅድም ነበር… በእውነት ተናዶብኝ ነበር!

## ያለ ዕድሜ ጋብቻ

### ዕድሜ በጋብቻ ፣ እና የጋብቻ ዓይነት

በመካከለኛ ደረጃ መረጃ በሚሰበሰቡበት ወቅት በናሙና የተወሰዱት አማካኝ ሴት ተሳታፊዎች በመካከለኛው የታዳጊነት ዕድሜ ላይ ብቻ (በአፋር 16 አመት እና በሶማሊ 15.7 አመት) ስለነበሩ ትዳር መመሥረት እምብዛም አልነበረም፡፡ በሁለቱም ክልሎች ጥናቱ ከተካሄደባቸው

ምስል 9: የአሳዳጊዎች እምነት ስለ ሴት ልጅ ግርዛት፣ በጾታና በክልል




ወጣት ሴቶች መካከል ያገቡ 5% ብቻ ነበሩ። በአፋር ክልል ያገቡ ልጃገረዶች በአማካይ በ17.3 ዓመታቸው በአማካይ በ4.6 ዓመት ከሚበልጧቸው ወንዶች ጋር ነበር። ከሞላ ጎደል ሁሉም (95%) የአፋር ሙሽሮች ጋብቻቸው የተወሰነው በወላጆቻቸው አማካኝነት ሲሆን ይህም በአብሱማ ባህል መሰረት የትዳር አጋሮች በእናታቸው በኩል የአጎት ልጆች መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል። ልጃገረዶች በትዳር ጓደኛ ምርጫ ወይም የጋብቻ ጊዜ በመወሰን ሂደት ውስጥ ምንም አይነት ተሳትፎ የላቸውም። አንዲት የ21 ዓመት እናት አፋር እንዲህ በማለት ታስታውሳለች።

እሱን [ባሏን] ስለማግባቴ የሰማሁት በሠርጉ ቀን ነው። ያዙኝ እና በዛው ቀን ነገሩኝ... እንዳገባ የወሰነው አባቴ ነው።

በሶማሊ ክልል ያለው የጋብቻ ባህል በጣም የተለየ ነው። ያገቡ ልጃገረዶች ጋብቻ የፈፀሙት ቀደም ብለው (በአማካኝ 16 አመት እድሜያቸው) ሲሆን፣ በተጋቢዎቹ መካከል ያለው የዕድሜ ልዩነት ትንሽ (2.2 ዓመት) ነበር። ሁሉም ጋብቻዎች (94%) ማለት ይቻላል የተወሰኑት በራሳቸው በሁለቱ ወጣት ተጋቢዎች ነበር። በ15 ዓመቷ ያገባች አንዲት የ18 ዓመት የሶማሊ ወጣት፣ የትዳር ምርጫዋን ስትገልጽ፣ "ቤተሰቦቼ ስለ ጉዳዩ ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም። እኔ በራሴ ወሰንኩ።" ብላለች።

## ስለ ያለ ዕድሜ ጋብቻ ያሉ አዝማሚያዎች

በአጋማሽ ጥናቱ ላይ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች ትዳር መመሥረት እምብዛም ባይሆንም፣ ይህ ጥናት እንደሚያሳየው በሁለቱም ክልሎች በሚገኙ የምርምር ቦታዎች ያለ ዕድሜ ጋብቻ የተለመደ ብቻ ሳይሆን ዋና መለያ ነው ተብሎ ይታመናል። በአፋር (84%) እና በሶማሊ (83%)፣ ከአራት አምስተኛ በላይ የሚሆኑ አሳዳጊዎች አብዛኞቹ የማህበረሰቡ ልጃገረዶች ከ18 ዓመታቸው በፊት እንደሚያገቡ ገልጸዋል (ምስል 10ን ይመልከቱ)። በሶማሊ ክልል፣ ብዙ ወጣቶች (75%) በዚህ ተስማምተዋል። የአፋር ወጣቶች ያለ ዕድሜ ጋብቻ የተለመደ ነው ብለው የማመን ዕድላቸው አነስተኛ ሲሆን፣ ከነዚህ 60% 'ብቻ' የሚሆኑት፣ አብዛኞቹ ልጃገረዶች የሚያገቡት ከ18 ዓመታቸው በፊት ነው ብለው ያምናሉ።

ስለ ያለዕድሜ ጋብቻ መስፋፋት ያለው እምነት በተለይ ከእናቶች ገጠመኝ ጋር ሲጣመር በጣም አስደሳች ነው። በአፋር የምርምር ቦታዎች 88% የሚሆኑት እናቶች ያገቡት ከ18 ዓመታቸው በፊት ነው። በሶማሊ የምርምር ቦታዎች ይህ አሃዝ 58% ብቻ ነበር። ጥናቱ እንደሚያመለክተው በያለዕድሜ ጋብቻ መስፋፋት ላይ ያሉ እምነቶች በአገር አቀፍ ሕግ መሠረት ያለዕሜ ጋብቻ ሕገ-ወጥ መሆኑን በማወቅ በአንፃራዊነት የማይታለፉ ናቸው።[6] በተለይ በሶማሊ ክልል 13% ያህሉ ወጣቶች ብቻ ህጉን እንደሚያውቁ ገልጸዋል (ምስል 11ን ይመልከቱ)።

አይነታዊ ጥና ለእነዚህ የዳሰሳ ጥናቶች ግኝቶች ልዩነትን ይጨምራል። በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች ከግማሽ ያነሱ ወጣት ሴቶች (47%) ትምህርት ቤት ገብተዋል፤ ምክንያቱም ሁሉም የገጠር ማህበረሰቦች ትምህርት ቤት ስለሌላቸው፣ ልጃገረዶች ውሃ የመቅዳት ኃላፊነት ስላለባት እና ወላጆች ብዙውን ጊዜ፣ አንዲት እናት እንደተናገረችው "ሴት ልጆችን ወደ ትምህርት ቤት መላክ ወደ ጋለሞታነት ይለውጣቸዋል"' ብለው ስለሚያስቡ ነው። በቅርብ ዓመታት ውስጥ ያለ ዕድሜ ጋብቻ የተለመደ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ወጣቶች ለማግባት ሲወስኑ የሚያገቡበት ዕድሜው እያሽቆለቆለ መምጣቱን ጭምር ምላሽ ሰጪዎች ተናግረዋል። አንድ የሶማሊ የጎሳ መሪ እንደገለጹት፡


አብዛኛዎቹ ልጃገረዶች 18 ዓመት ሳይሞላቸው ያገቡ


6 የክልል መንግስታት ይህንን ህግ እስካሁን አላፀደቁትም።

ናቸው…" 70% የሚሆኑት ጋብቻዎች ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ግለሰቦችን እንደሚያካትቱ እገምታለሁ።

የዚያ ክልል አንድ የቀበሌ ሊቀ መንበር አክለውም፣ "እድሚያቸው 10፣ 12 እና 13 የሆኑ ልጃገረዶች ሲያገቡ አይቻለሁ።' ብለዋል። በሌላ በኩል በአፋር የምርምር አካባቢዎች፣ በተለይ ወላጆች የሴት ልጅ አካላዊ እድገት፣ የወር አበባ መጀመር ትኩረት በሚሰጡበት ገጠራማ አካባቢዎች ብዙዎቹ ልጃገረዶች የሚያገቡት ለአቅመ ሄዋን ከመድረሳቸው በፊት ነው። በነዚህ የምርምር ቦታዎች ውስጥ ያለው የጋብቻ ዕድሜ በአጠቃላይ ከልጃገረዶች የትምህርት ቤት መግባት (67%) እና ወላጆች ስለ አደጋዎች ግንዛቤ ጋር አብሮ እያደገ ነው። የ18 ዓመቱ ወጣት ከአፋር እንዲህ ሲል ገልጿል። ቀደም ባሉት ጊዜያት በአካባቢያችን ያሉ ልጃገረዶች በለጋ እድሜያቸው በ13፣ 14 ወይም 15… አመታቸው አግብተዋል። አሁን ግን በመንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የሃይማኖት መሪዎች እና የሸሪዓ አባቶች ባደረጉት ጥረት የሴቶች የጋብቻ ዕድሜ ትንሽ ከፍ ብሏል። አሁን እዚህ ያሉ ልጃገረዶች የሚያገቡት 17 ዓመት ከሞላቸው በኋላ ነው።

የልጃገረዶች የትምህርት ተደራሽነት በተለይ ያለዕድሜ ጋብቻን በመቀነስ ረገድ ለተመዘገበው እድገት አስፈላጊ መሆኑን የአፋር ምላሽ ሰጪዎች ጠቁመዋል። ትምህርት



ቤቶች ሴት ልጆች ያለ ዕድሜ ጋብቻ ህገወጥ እንደሆነ፣ እምቢ የማለት መብት እንዳላቸው እና ያለ እድሜ እርግዝና አደገኛ መሆኑን ያስተምራሉ። እንዲሁም ለያለ ዕድሜ ጋብቻ የታጩ መሆናቸውን በሰዐቱ ሪፖርት የሚያደርጉበት ቦታ ያመቻቹ ሲሆን ይህን እንዳሳወቁ ጋብቻው እንዲሰረዝና በተማሪነታቸው እንዲቀጥሉ ያደርጋሉ። አንዲት የ18 ዓመ የአፋር ክልል ነዋሪ የሆነች ያላገባች ወጣት ሁኔታው እንዴት እንደሆነ ገልጻለች።

የ9ኛ ክፍል ተማሪ ሳለሁ ጀምሮ እንዳገባ ጠየቁኝ። ለሦስት ዓመታት ያህል እንዳገባ ሲጠይቁኝ ነበር ነገር ግን አባቴ ሊድረኝ አልፈለገም። ተማሪ ስለሆነች ትምህርቷን ከጨረሰች በኋላ እንድታገባ ነው የምፈልገው አለ።

በአፋር ክልል የሚገኙ በርካታ ምላሽ ሰጪዎችም በተለይ ልጃገረዶች እምቢ ሲሉ የሃይማኖት አባቶች ያለ ዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል የሚያደርጉትን ጥረት አድንቀዋል። በእርግጥም በከተሞች አካባቢ ወላጆችና የቀበሌ አስተዳዳሪዎች ልጆች ያለዕድሜያቸው እንዲያገቡ በማስገደድ በተጫወቱት ሚና ምክንያት እንዲታሰሩ በማድረግ አንድ የሃይማኖት መሪ ከወረዳ አመራሮች ጋር አብሮ እንደሰራ አንድ ምላሽ ሰጪ ተናግሯል።

### በጋብቻ ዕድሜ የታዳጊዎች ምርጫዎች

አብዛኞቹ ልጃገረዶች የሚያገቡት ለአቅመ ሄዋን ከመድረሳቸው በፊት እንደሆነ ቢያምኑም፣ በጥናቱ ላይ የተሳተፉ በአፋር ክልል (88%) እና ሶማሊ ክልል (84%) አብዛኞቹ ወጣቶች በግላቸው ለአቅመ ሄዋን ሲደርሱ ማግባት እንደሚመርጡ ተናግረዋል። በአፋር ይህ ምርጫ በአብዛኛው ጋብቻዎች የሚካሄዱብትን ሁኔታ ተከትሎ የሚመጣ ነው። በታዳጊነት ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶች በጋብቻ ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ምንም ሚና የላቸውም፤ የሚያገቡትን ሰውና የሚያገቡበትን ጊዜ ወላጆቻቸው (ብዙውን ጊዜ አባታቸው) ሲወስኑ ነው፤ እንዲሁም ይህን ለማድረግ ከትምህርት ቤት እንዲወጡ ማድረግ ያልተለመደ አይደለም። በሌላ መልኩ፣ በጎልማሳነት ዕድሜ ላይ የሚያገቡ ልጃገረዶች ሰውነታቸው ከመብሰሉ በፊት በሚፈጠር እርግዝና ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉትን አደጋዎች ማስቀረት ብቻ ሳይሆን፣ የተኛውን የአጎት ልጅ እንደሚያገቡ ጭምር የሚሉት ይኖራቸዋል። አንድ አባት ልጃገረዶች ብዙውን ጊዜ በዕድሜ የሚበልጣቸውን የአጎት ልጆችን ለጋብቻ እንደማይቀበሉ እንዲህ በማለት ገልጸዋል።

በአሁኑ ጊዜ ልጃገረዶች እና ሴቶች ስለመብታቸው ስለሚያውቁ የሴት ልጅ አብሱማ የሆነ ሽማግሌ ልጃገረድ ማግባት ከፈለገ እምቢ ትላለች… ልጃገረዶች አሁን በዕድሜ እኩያቸው የሆኑ ወጣት ወንዶችን ማግባት ይፈልጋሉ።

በሶማሊ ክልል የምርምር ቦታዎች፣ ወጣቶች በጎልማሳነት ዕድሜ ለሚያደረግ ጋብቻ ያላቸው ምርጫዎች ከሰፊው ትርክት በተቃራኒ ጎልተው ይታያሉ። ይህም ወላጆች ጋብቻን ለማዘግየት በሚሞክሩበት ጊዜም እንኳ፣ ታዳጊዎች ለመስማት ፈቃደኞች አይደሉም፤ ምክንያቱም በአብዛኛው በጓደኞቻቸው መካከል የአዋቂነት ደረጃን ለመግለጽ የተሻለው መንገድ አድርገው ስለሚመለከቱት ነው። በ15 ዓመቷ ያገባች የ20 ዓመቷ ወጣት ወላጆቿን ችላ ብላ እንደነበር እንዲህ ስትል ታስታውሳለች።

በጥሩ ሁኔታ ሳድግ ማግባት እንደምችል ወላጆቼ ማግባት እንደሌለብኝ ነገሩኝ… ለወላጆቼ ጋብቻ በፈጣሪ ፈቃድ እንደሚሆን ነገርኳቸው። ጋብቻ የሚወሰነው በፈጣሪ ነው…

በ11 ዓመቱ በአንድ አመት የምታንሰውን ሴት ያገባ የ20 ዓመት ወጣት ምርጫው የተቀረፀው እኩዮቹን በማየቱ እንደሆነ ገልጿል። ትዳር ጥሩ ነገር እንደሆነ እናውቃለን። ሁሉም ሰው ያውቃል። ሰዎች ሲጋቡ እናያለን፣ ከዚህ በፊትም ሰርግ ላይ ተገኝተናል።' ከአፋር ክልል በተለየ መልኩ በሶማሊ ክልል ያሉ የሀይማኖት አባቶች ያለ ዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል ጣልቃ መግባታቸውን በአይነታዊ ምርምሩ ምንም አይነት መረጃ አላገኘንም። በእርግጥም ብዙዎቹ ወጣት ባለትዳሮች ከጋብቻ በፊት ከሚደረግ ግብረ ስጋ ግንኙነት ይልቅ ያለ ዕድሜ ጋብቻ እንደሚመረጥ ስለሚያምኑ ከቸኮላ ትዳር ለማሳመን እንደማይሞክሩ ገልጸዋል።

### ማጠቃለያዎች

ካሁን በፊት ከተሰሩ ጥናቶች አኳያ፣ የጊጅ ጥናት እንደሚያሳየው የሴት ልጅ ግርዛት በአፋር እና በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች ላሉ ልጃገረዶች ላይ ሁሉ እንደሚቀጥል፣ ምንም እንኳን ልጃገረዶች የሚገረዙበት ጊዜ ቢለያይም፣ በሶማሊ ናሙና ውስጥ ያሉ ሁሉም በታዳጊነት ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶች ግርዛቱን ገና አልፈጸሙም።

ምላሽ ሰጪዎች አሁን ያሉትን ድርጊቶች የሚገነዘቡት በአብዛኛው እጅግ በጣም ከተስፋፉ ባህላዊ ልምዶች ጋር የተያያዘ በመሆኑ፣ እና በተለይ በከተማ አካባቢ ያሉት አሁን ያለውን አሰራር ሱና (የተፈቀደ) እንዲሆን ለማድረግ ስለሚጨነቁ፣ የሴት ልጅ ግርዛት አይነት በሁለቱም ክልሎች አከራካሪ ጉዳይ ነው። ምንም እንኳን አብዛኛው የሁለቱም ክልሎች ልጃገረዶች ብልት መጥበብ ቢደርስባቸውም፣ ከመጠበቡ በፊት የተወገደው ሥጋ መጠን እና የመጠበቡ መጠን በመንግስት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የኃይማኖት አባቶች የተብብር ጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ ቀስ በቀስ 'እየተሻሻለ' ይመስላል።

በክልሎች መካከል ያለው ልዩነት ቢኖርም (በአፋር የጥናት ጣቢያዎች ውስጥ ያሉ ምላሽ ሰጪዎች በአጠቃላይ የሴት ልጅ ግርዛትን ጉዳት የሚያውቁ፣ ድርጊቱን ለመቀጠል የመደገፍ ዕድላቸው አነስተኛ የሆነ እና ለ«መለስተኛ» የግርዛት ዓይነቶች የመጠቀም ዝንባሌያቸው ከሶማሊ አቻዎቻቸው የበለጠ ነው) በሁለቱም ክልሎች ውስጥ ባሉ የምርምር ቦታዎች ለድርጊቱ የሚደረገው ድጋፍ ጠንካራ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት የሴት ልጅ ግርዛት ሀይማኖታዊ ግዴታ ነው፣ ለባህል መባዛት አስፈላጊ ነው፣ እንዲሁም የሴት ልጆችን የወሲብ ስሜት በመቆጣጠር ለትዳር ተስማሚ ያደርጋቸዋል በሚለው እምነት ነው። በእርግጥ በሶማሊ የምርምር አካባቢዎች ጎልማሳ ሴቶች እና የወደፊት ሙሽሮች ብዙውን ጊዜ የሴት ልጅ ግርዛትን መደገፍ ብቻ ሳይሆን በተለይ የሴት ልጅ ብልት መስፋት ድንግል መሆኗን ለማረጋገጥ ብቸኛው መንገድ እንደሆነ ይገልጻሉ። በሶማሊ፣ እንዲሁም አንዳንድ የሕክምና ማስረጃዎችን (የሴት ልጅ ግርዛት እና የተሰፋን



የአፋር ሙሽሪት እና ጓደኛዋ © ናታሊ በርትራምስ /ጌጅ 2025

የሴት ልጅ መቅደድ) ያገኘን ሲሆን ጎልማሶችና ወጣቶች የሴት ልጅ ግርዛት ሙሉ በሙሉ የሴቶች መገለጫ እንደሆነ ይስማማሉ። በአፋር ክልል፣ አባቶች ለሴት ልጆቻቸው የግርዛት አይነት የመወሰን ሚና የነበራቸው መሆኑን እና ድርጊቱን ሙሉ በሙሉ ለመተው ፈቃደኞች መሆናቸውን አይተናል።

የአጋማሽ ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት የናሙናችን አማካይ ወጣት ዕድሜ ገና 16 ዓመት ያልሆነው በመሆኑ ያገቡ ጥቂቶች ብቻ ነበሩ። መካከለኛ የታዳጊነት ዕድሜ ላይ ባሉ የወር አበባ ማየት በጀመሩ ወይም 15 ዓመት በሞላቸው ልጃገረዶች ላይ ያለ ዕድሜ ጋብቻ ስለሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ መሆኑ በሁለቱም ክልሎች ሰፊ ስምምነት (በተለይም በሩቅ አካባቢ) ያለ በመሆኑ ምክንያት ይህ በማጠናቀቂያ ጥናቱ ወቅት ይለወጣል ብለን እንጠብቃለን። በሁለቱም ክልሎች ልጃገረዶች ለያለ ዕድሜ ጋብቻ ተጋላጭ የመሆናቸው ምክንያቶች በጣም የተለያዩ ናቸው። በሁለቱም ክልሎች ጎልማሶች እና ወጣቶች ስለ ጋብቻ ህግ ያላቸው ግንዛቤ ውስን ነው። በአፋር ክልል ምላሽ ሰጪዎች እንደገለፁት የአብሱማ ባህል በሚከተሉ በወላጆች ምክንያት ያለ ዕድሜ ጋብቻ የተለመደ ነው። ሆኖም ግን፣ የልጃገረዶች ለመደበኛ ትምህርት በተሻሻለ ተደራሽነት ምክንያት ለሴቶች ልጆች (እና መምህራኖቻቸው) የጋብቻ ዕድሜን ማዘግየትና ለመደገፍ እና ልጃገረዶች የትዳር አጋራቸውን እንዲመርጡ የማሳመን እድሉ እያደገ መጥቷል። በሶማሊ የሃይማኖት መሪዎች ሴት ልጆች ገና ልጅ ቢሆኑም ጋብቻን ማፅደቅ መብታቸው ነው ቢሉም፣ ሌሎች ምላሽ ሰጪዎች ያለ ዕድሜ ጋብቻ በወንዶች ልጆችም በልጃገረዶችም የተለመደ እየሆነ በመምጣቱ ላይ እንዲሁም ጋብቻ የሚፈጸምበት ዕድሜ እየቀነሰ በመምጣቱ ላይ ተስማምተዋል።

## የፖሊሲና ፕሮግራሚንግ አንድምታዎች

የኢትዮጵያ መንግስት እና የልማት አጋሮቹ ያለ ዕድሜ ጋብቻን እና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት በወጣው ብሔራዊ ፍኖተ ካርታ ላይ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት እንዲሁም ጐጂ ልማዶችን በማስወገድ ላይ ያተኮረውን የዘላቂ ልማት ግብ እንዲያሳኩ ከተፈለገ፣ የጥናታችን ግኝቶች በርካታ ቁልፍ ተግባራትን ይጠቁማሉ። ጥረቶች በሴክተሮች በጥሩ ሁኔታ የተቀናጁና እርስ በእርስ የሚደጋገፉ መሆናቸውን በመገንዘብ በታዳጊነት ዕድሜ ላይ ያሉ ልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች ፈጣን ለውጦች ለመከታተል የሚያስፈልጉትን ተዋናዮች እና በተሰጣቸው ኃላፊነት ውስጥ ያሉትን የተለዩ ተግባራትን እናሳያለን።

### ሴቶችና የማህበራዊ ጉዳዮች ዘርፍ

የአፋር እና የሶማሊ ክልል መስተዳድሮች የሴት ልጅ ግርዛትን እና የልጅ ጋብቻን ለማስቆም በቂ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ ባለመቻላቸው እና የፍትህ ሴክተሩ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመቅረፍ በበቂ ሁኔታ ቅድሚያ ባለመስጠቱ ምክንያት የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ዘርፍ እነዚህን አሠራሮች ለመቅረፍ ክልላዊ ብጁ ዕቅዶችን ለማዘጋጀትና ለመቆጣጠር ከፍትህ፣ ከትምህርት፣ ከጤና፣ ከግብርናና ከአደጋ ሥጋት አስተዳደር ዘርፎች የተውጣጡ የሥርዓተ ፆታ ባለሙያዎችን ያካተተ አዲስ ዘር-አቀፍ የመንግሥት አካል በመሰብሰብ መቆጣጠር አለበት።

ገደብ የለሽ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች የሴት ልጆችን እና የሴቶችን የትምህርት፣ የስራ እና የውሳኔ ሰጪነትን እድል ስለሚገድቡ፣ በመጨረሻም የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ

ዕድሜ ጋብቻን ስለሚገፋፉ፣ በሁሉም ደረጃዎች የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ዘርፍ እነዚህን እምነቶች እና ልማዶች በቀጥታ ለመፍታት ቅድሚያ መስጠት አለበት። ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡

- ልጃገረዶች እና ሴቶች የመብት ጥሰቶችን በሚስጥር ሪፖርት የሚያደርጉባቸው ቦታዎች ማመቻቸትና ማጠናከር
- የራሳቸው እና የወደፊት ሴት ልጆቻቸውን መብት እና ጥሰቶችን በሚስጥራዊ በሆነ መንገድ እንዴት ሪፖርት እንደሚያደርጉ (ለምሳሌ ለአስተማሪዎች፣ ለሴቶች ጉዳይ፣ ለፖሊስ እና ለፍትህ አካላት) የልጃገረዶችን እና የሴቶችን ግንዛቤ ለማሳደግ ለሚደረጉ ጥረቶች ቅድሚያ መስጠት
- ልጃገረዶች እና ሴቶች (መደበኛ ትምህርት ማግኘት ለተከለከሉት) ማንበብና መጻፍን ጨምሮ የራሳቸውን ችሎታዎች ማዳበር የሚችሉባቸውን መንገዶች መፍጠር፤
- የልጆች አስተዳደግ ትምህርት ኮርሶችን ጨምሮ፣ ሴት ልጆቻቸውን ለማበረታታት እና ያልተገረዙ ልጃገረዶች ባል እንደማያገቡ የሚያሳዩ ደንቦችን ማስወገድን ጨምሮ ወንዶች ልጆቻቸው አማራጭ የወንድነት ባህሪን እንዲከተሉ ለማበረታታት ከእናቶች ጋር መስራት፤
- ስለልጃገረዶች ትምህርት አስፈላጊነት ግንዛቤን ማሳደግ እና ትምህርታቸውን በተጨባጭ እንዴት እንደሚደግፉ፣ የጊዜ አጠቃቀም ፍላጎቶችን ማስተዳደር እና ከሌሎች ቤተሰቦች ጋር ደህንነቱ የተጠበቀ መንገድ ወደ ትምህርት ቤት የሚሄዱበትን ሁኔታ ማመቻቸትን (ለምሳሌ በቡድን ወይም ከአዋቂ ጋር መሄድን) ጨምሮ ከማህበረሰቡ ጋር መስራት፤
- በማህበረሰቡ ውስጥ የሴቶችን ከሴት ልጆች ወሲባዊ ንፅህና እና "የተሳካ" ጋብቻ አመለካከት ለማላቀቅ መስራት፤
- ለውሳኔ አሰጣጥ ተጠያቂነት እንዲኖር የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ክልላዊ በሆነ መንገድ ማስተካከል (ለምሳሌ በሶማሊ ክልል የሴት ልጅ ግርዛት ዘግይቶ የሚካሄድ ስለሆነ ልጃገረዶች በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ሚና አላቸው፣ እንዲሁም በዚያ ክልል ውስጥ ጋብቻዎች ብዙውን ጊዜ በታዳጊዎች የሚወሰኑ ናቸው፤ በአፋር ክልል ደግሞ የሴት አያቶች ግርዛት ላይ የበለጠ ተጽዕኖ ያሳድራሉ)፤ ልጃገረዶችን ቤተሰቦቻቸውን እና ማህበረሰቡን የሁለቱም ጎጂ ልማዶችን ጉዳት በማስተማር ስለ ጎጂ ልማዶች ጥቅም ያላቸውን ግንዛቤና ደንቦችን በመቃወም ግንዛቤን ማሳደግ፤
- በማህበረሰቡ ውስጥ እና በማህበራዊ ሚዲያው የለውጥ አርበኞች ሆነው መሥራት የሚችሉ የተማሩ ልጃገረዶችና ሴቶች እና ተራማጅ ወንዶች ልጆችና እና ወንዶችን ያካተተ አርአያ የሆኑ ካድሬዎችን ማቋቋም፤
- በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃትን መከላከልና የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ፣ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች የደረሰባቸውን በተሻለ ሁኔታ መደገፍ እንዲችሉ፣ በግጭት ለተጎዱ አካባቢዎች ቅድሚያ መስጠት፣ እና እንዲሁም ከአገልግሎት ሰጪዎች ጋር በአንድ ቦታ ማዕከላት በመስራት ፍቃዳቸውን በማስፋት ያለ ዕድሜ ጋብቻ እና የሴት ልጅ ግርዛት አደጋ ላይ ያሉትን ለመደገፍ ድጋፍ መስጫ የአንድ ቦታ ማዕከላትን ማስፋፋት፤
- ከሌሎች የመንግስት ዘርፎች ጋር በመተባበር ብሄራዊ እና ክልላዊ ህጎችን ማስማማት እና ሀራም የሆነ የትኛውም የሴት የአካል ክፍል እንዳይሌለ የሚገልጽ ቋንቋን ለማካተት የ2023 ፈትዋ ማጠናከር እና ማራዘም።

አባቶች፣ ወንድሞች፣ ወንድ አኩዮች፣ የወንድ ጓደኞች እና ባሎች ግርዛትን ጨምሮ ልጃገረዶችን እና ሴቶችን የሚጎዳውን ሰፊ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ለማስቀጠል ተባባሪ ስለሆኑ፣ የወንድ አመለካከቶችን እና ልምዶችን ለመቀየር በትምህርት ቤት እና በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ የተሳትፎ ክፍል ጊዜዎችን እና የሚዲያ ዘመቻዎችን ለመጠቀም የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሴክተር ከትምህርት ሴክተሩ እና ህጻናት እና ጾታን ያማከለ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ መሥራት አለበት። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል።

- ልጃገረዶች የማጥፒያ ጊዜ እንዲኖራቸው ሚስቶችን እና እህቶችን እንዴት በተሻለ ሁኔታ መደገፍ እንደሚችሉ የአባቶችንና ወንድሞችን ግንዛቤን ማሳደግ፤
- የሴት ልጅ ግርዛት የተፈፀመባትን ሴት ማግባት ጠቃሚ ያልሆነበትን ምክንያት ወንዶች እና ወንዶች ልጆች እህቶቻቸውን እና ሴቶች ልጆቻቸውን ከግርዛት ጋር የተያያዘ ጉዳት እንዳይደርስባቸው እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ ወንዶችን እና ወንዶች ልጆችን ማስተማር፤
- በማህበረሰቡ ውስጥ ወንዶችን ከሴት ልጆች ወሲባዊ ንፅህና እና "የተሳካ" ጋብቻ አመለካከት ለማላቀቅ መስራት፤
- ወንዶችንና ወንዶች ልጆችን ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ሚስት ተግባራዊ ጥቅሞችን (ለምሳሌ የተሻለ ረዳት እንደሆነች፣ በወሊድ ጊዜ የሚደርሱ ጉዳቶች አነስተኛ እንደሚሆኑ) እና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰችን ልጅ ማግባት የሚያስከትለውን ጉዳት (ለምሳሌ ቶሎ ፍቺ የመከሰት እድል፣ ልጅ የማሳደግ ተግዳሮቶች፣ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አለመጣጣም አደጋ) ማስተማር፤
- የበለጠ ፍትሃዊ የሆነ የቤተሰብ ውሳኔ አሰጣጥ እና የስራ ጫና እንዲኖር ማበረታታት፤ እና ሃይለኛ ወንዶችን መንቀፍ።

የሴት ልጅ ግርዛት በአፋር እና በሶማሌ ክልሎች እንደ ሀይማኖታዊ ግዴታ ስለሚታይ እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ በሃይማኖት ተቀባይነት ያለው፣ እንዲያውም ተመራጭ ተደርጎ ስለሚታይ፣ የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ እና የፍትህ ሴክተሮች መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ተቀራርበው በመስራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ጉዳት ለመቀነስ እና በመጨረሻም እነዚህን ጎጂ ልማዶች ማስቀረት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል።

- ስለ ሴት ልጅ ግርዛትና ያለ ዕድሜ ጋብቻ ማቀንቀን ሕገ-ወጥ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጃገረዶች ኒካህ (የሸሪዓ ጋብቻ የምስክር ወረቀት) እንዲያስሩ በማድረግ ያለ ዕድሜያቸው እንዲያገቡ በማድረጋቸው በህግ ሊጠየቁ እንደሚችሉ የሃይማኖት መሪዎችን ግንዛቤ ማሳደግ፤

- የሃይማኖት መሪዎች ወጣት ሴቶችን ዝምታቸውን ከመቀበል ይልቅ ለትዳር ስምምነታቸውን እንዲጠይቁ ማበረታታት፤
- ስለ ሴት ልጅ ግርዛት (በተለይ ብልት መስፋት) እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ ጉዳቶች እንዲሁም ጋብቻን እስከ ጎልማሳነት ዕድሜ ማዘግየት ያለውን ጥቅሞች ትምህርት መስጠት፤
- ማህበረሰቦችን የትኞቹ ድርጊቶች ሱና (የተፈቀዱ) እና የትኛዎቹ ልማዶች ደግሞ ሀራም (የተከለከሉ) እንደሆኑ ማስተማር።
- የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ሃይማኖታዊ ገጽታዎች ለማብራራት ብሔራዊ ምክክር መጥራት፣ እነዚህን ድርጊቶች እንዴት መፍታት እንደሚቻል (የሴት ልጅ ግርዛት ወደ አልተስፋፋባቸው አብዛኛዎች ሙስሊም አገሮች ጉዞዎችን ማዘጋጀትን ጨምሮ) እና ድርጊቶቹን ለማስቆም ያለመ የተቀናጀ የዘመቻ ስልቶችን ማዘጋጀት፣
- ለልጃገረዶችና ለወደፊት ትውልድ የትምህርት ድጋፍ መገንባት፤
- ገደብ የለሽ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን መፍታት፣ ልጃገረዶች እና ሴቶች ለቤተሰብ እና ማህበረሰቦች የሚያበረክቱትን እሴት ማወቅን ጨምሮ፣ ወንዶች እና ወንዶች ልጆች ከሴት ልጅ ጥቃት እንዲርቁ፣ ሴት የቤተሰብ አባላትን በደግነት እና በአክብሮት እንዲይዙ ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ።

ጎሳ እና ባህል የአፋር እና የሶማሌ ማንነት እንዲሁም የሴት ልጅ ግርዛት እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን የማስቀጠል መነሻ በመሆናቸው፣ ልጃገረዶችን እና ሴቶችን የሚጎዱ እምነቶችን እና ልምዶችን ለመቀየር የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሴክተሩ ከትምህርት ሴክተሩ እና ከህፃናት እና ጾታ ተኮር ስራ ከሚሰሩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ከጎሳ መሪዎች ጋር በቅርበት ለመስራት መተባበር አለባቸው። ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

- የሴቶችን ትምህርት ማሳደግ፤
- በራዲዮ፣ በማህበራዊ ሚዲያ፣ በቴሌቪዥን፣ በማህበረሰብ ውይይቶች፣ ትምህርት ቤትን መሰረት ባደረጉ የስርዓተ-ፆታ ክለቦች እና በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የቤት ለቤት ጉብኝትን ጨምሮ ስለ የሴት ልጅ ግርዛት በተለይም ስለ ብልት መስፋት ጉዳት በተቀናጀ መልኩ ግንዛቤን ማሳደግ፤
- ያለ ዕድሜ ጋብቻ ጉዳቶችን እና ጋብቻን እስከ ጎልማሳነት ዕድሜ ማዘግየት ያለውን ጥቅም ግንዛቤ ማሳደግ፤
- ማህበረሰቦች - በተለይም ባህላዊ ገራዦች እና እናቶች - ሁሉም አይነት የሴት ልጅ ግርዛት ህገ-ወጥ መሆናቸውን እና በገንዘብ እና በእስራት የሚያስቀጣ መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ።



የ15 ዓመቷ የአፋር ልጃገረድ ቡና ስታፈላ © ናታሊ በርትራምስ /ጌጅ 2025




በሶማሌ ጤና ጣቢያ የቀበሌ ስራ አስኪያጅ © ናታሊ በርትራምስ /ጊጅ 2025

## የፍትህ ሴክተር

የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ስለሚከለክለው ህግ ያለው እውቀት እንደ ህጉ አፈጻጸም ውስን በመሆኑ፣ የፍትህ ሴክተሩ በጎጂ ልማዶች ላይ የተደነገጉ ሀገራዊ ህጎችን ለማስተዋወቅ እና ለማስከበር ጥረቶችን ማሳደግ አለበት። ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

- በሰብአዊ መብቶች ላይ ከተመሰረቱ ድርጅቶች (የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን እና የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ጨምሮ) በጋራ መስራት፣ ከክልል ባለስልጣናት እና ህግ አውጪዎች ጋር የክልል ህጎች ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ከሚከለክሉ ሀገራዊ ህጎች ጋር እንዲጣጣሙ እና የቤተሰብ ህጉን በማፅደቅ እነዚህ ድርጊቶች በወንጀል እንዲታዩ በጋራ መስራት፤
- የልጃገረዶችን እና የሴቶችን የትምህርት፣ የውርስ እና ከጥቃት (ከሴት ልጅ ግርዛት፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻን እና ከቅርብ አጋር ጥቃት ጨምሮ) ነፃ የመሆን መብቶች ለማሻሻል ከሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጋር መስራት፤ በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች እና በመደበኛ ፍርድ ቤቶች እና የፍትህ ስርዓት መካከል ያለውን ትብብር ማሳደግ።
- በሴት ልጅ ብልት መስፋት ለመቃወም እ.ኤ.አ. በ2023 የወጣውን ፈትዋ በማስፋፋት የትኛውም የሴት ልጅ የአካል ክፍል ሀራም እንዳልሆነ የሚገልጽ ቋንቋ እንዲጨምር ከሌሎች የመንግስት ሴክተሮች፣ ከብሔራዊ የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን የማስቆም ህብረት እና ከኢትዮጵያ የሃይማኖት ምክር ቤት ጋር በመስራት፤
- ከባህላዊ እና ማህበረሰብ መሪዎች ጋር በመስራት ማህበረሰቡ ሁሉም አይነት የሴት ልጅ ግርዛት ህገወጥ መሆኑን አውቆ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጉዳቱን በመቀነስ ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ እና በረዥም ጊዜ ውስጥ ይህ ሂደት ረጅም እና ቀጥተኛ ያልሆነ ሂደት መሆኑን በመገንዘብ ድርጊቱን ወደ ማጥፋት መሸጋገር እንዳለበት ማሳሰብ።
- ከባህላዊ እና የማህበረሰብ መሪዎች ጋር በመስራት ማህበረሰቦች ሁሉም አይነት ያለ ዕድሜ ጋብቻዎች- በታዳጊዎቹ ፍላጎትም ቢሆን - ሕገ-ወጥ መሆናቸውን እንዲያውቁ ማድረግ፤
- የታቀዱ የሴት ልጅ ግርዛትንና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል እና በቅርብ ጊዜ የተፈጸሙ ጋብቻዎችን ለመሰረዝ ስለሚረዱ በትምህርት ቤቶች እና በሌሎች ቦታዎች ሚስጥራዊ የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴዎችን ማቋቋም፣
- በወላጆች፣ በባህላዊ ገራዥዎች፣ በአዋቂዎች ባሎች እና በጋብቻ አስፈጻሚዎች፣ በሌሎች አካባቢዎች ለሚፈጸሙ ጥሰቶች ቅጣቶች እንዲጣሉባቸው ከማህበረሰቡ ጋር መስራት፤
- ተፈጻሚነት ያላቸውን ቅጣቶች ለመወሰን ከማህበረሰቡ ጋር በመተባበር ከልጃገረዶች እና ሴቶች ጋር በመስራት የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ ስለ መብታቸው እና ስለ ሴት ልጆቻቸው የወደፊት ሴት ልጆቻቸው መብቶቻቸውን እንዴት እንደሚጠይቁ ከእናቶች ጋር በመተባበር የሴት ልጅ ግርዛትን ቅጣት እንዲያውቁ ማድረግ፤
- በሴት ልጅ ግርዛት (አባቶች) እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ (የአዋቂ ባሎች እና አባቶች) ህጎችንና መጣስ የሚያስከትላቸውን ቅጣቶች የበለጠ እንዲያውቁ ለማድረግ ከወንዶች እና ከወንዶች ልጆች ጋር በመስራት።

የሴት ልጅ ግርዛት እንደ ሀይማኖታዊ ግዴታ የሚታይ በመሆኑና ያለ ዕድሜ ጋብቻ በሃይማኖት ተቀባይነት ያለው፣ እንዲያውም ተመራጭ ተደርጎ ስለሚታይ፣ የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ እና የፍትህ ሴክተሮች መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ተቀራርበው በመስራት በአጭር ጊዜ ውስጥ ጉዳት ለመቀነስ እና በመጨረሻም እነዚህን ጎጂ ልማዶች ማስቀረት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል።

- ስለ ሴት ልጅ ግርዛትና ያለ ዕድሜ ጋብቻ ማቀንቀን ሕገ-ወጥ ስለመሆኑ፣ እንዲሁም ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጃገረዶች ኒካህ (የሸሪዓ ጋብቻ የምስክር ወረቀት) እንዲያስሩ በማድረግ ያለ ዕድሜያቸው እንዲያገቡ በማድረጋቸው በህግ ሊጠየቁ እንደሚችሉ የሃይማኖት መሪዎችን ግንዛቤ ማሳደግ፤
- ስለ ሴት ልጅ ግርዛት (በተለይም የሴት ብልት መስፋመስፋት) እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ የሚያስከትለውን ጉዳት እና ጋብቻን እስከ ጎልማሳነት ዕድሜ ማዘግየት ስላለው ጥቅም ትምህርት መስጠት፤
- ማህበረሰቦችን የትኞቹ ልምዶች ሱና፣ የትኞዎቹ ልምዶች ደግሞ ሀራም እንደሆኑ ማስተማር፤
- የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን በእስልምና ይፈቀዳሉ የሚለውን የተሳሳቱ አመለካከቶችን (ልጃገረዶች መስጊድ ለመግባት እና/ወይም ለመስገድ መገረዝ አለባቸው የሚለውን እምነት ጨምሮ) ማስተካከል እና ልማዶቹን ለማስወገድ አሳማኝ ሀይማኖታዊ ክርክሮችን ማዘጋጀት፤
- ለልጃገረዶችና ለወደፊት ትውልድ የትምህርት ድጋፍ መገንባት፤
- የተንሰራፋውን የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን መፍታት፣ ልጃገረዶች እና ሴቶች ለቤተሰብ እና ማህበረሰቦች የሚያበረክቱትን እሴት ማወቅን ጨምሮ፣ ወንዶች እና ወንዶች ልጆች ከሴት ልጅ ጥቃት እንዲርቁ፣ ሴት የቤተሰብ አባላትን በደግነት እና በአክብሮት እንዲይዙ ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ።

## የትምህርት ሴክተር

ሴት ልጆች ከወንዶች ይልቅ ከትምህርት የመገለል እድላቸው ከፍተኛ በመሆኑ፣ የሴቶች ትምህርት ሴት ልጆችን ለማብቃት እና የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ለማስቆም አስፈላጊ በመሆኑ፣ የትምህርት ሴክተሩ ሁሉም ሴት ልጆች ቢያንስ እስከ መለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጨረሻ እና እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቀቁ ለማድረግ ጥረቶችን ማሳደግ አለበት። ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

- ሁሉም ማህበረሰቦች (አርብቶ አደሮችን ጨምሮ) መሆናቸውን ጥራት ያለው ትምህርት ቢያንስ እስከ 6ኛ ክፍል የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ያሏቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ እና ትልልቅ ልጃገረዶች እና ሴቶች (ከዚህ ቀደም ትምህርት የተነፈጉ) ማንበብና መፃፍ እና የቁጥር እውቀትን የሚያገኙባቸውን እድሎችን ማስፋት።
- ከትምህርት ቤት ውጭ የሆኑትን ወይም በመደበኛነት ትምህርት ቤት የማይገኙ ልጆችን ለማስመዝገብ፣ ከትምህርት ለሚቀሩ ወላጆች ተመጣጣኝ ቅጣት ጨምሮ፣ ቤት ለቤት ቅስቀሳ ማድረግ፤
- በሥርዓተ-ፆታ ደንቦች፣ በወር አበባና በመፀዳጃ ቤት አጠቃቀም ዙሪያ ለሚከሰቱ መገለሎች ቀጥተኛ ትኩረት መስጠትን፣ የሴት ልጅ ግርዛትን፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻን እና ጾታዊ እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን ጨምሮ፤ ሥርዓተ ትምህርት እና ተጓዳኝ ሥርዓተ-ትምህርት (ለምሳሌ የልጃገረዶች እና የሥርዓተ-ፆታ ክለቦች) ማስፋፋት፤
- ለልጃገረዶች አዎንታዊ አርአያነት እንዲኖራቸው ብዙ ሴት አስተማሪዎችን መቅጠር፣፣
- ከድሀ ቤተሰቦች ለመጡ ተማሪዎች የበለጠ የትምህርት ቁሳቁስ አቅርቦትን ማረጋገጥ፤
- በሁሉም የክፍል ደረጃዎች፣ በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብሮች፣ የውሃና ንፅህና አጠባበቅ እና የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ አቅርቦቶች፣ አሳታፊ የሴቶች ክለቦች/የሥርዓተ-ፆታ ክለቦች፣ የመማሪያ መጽሃፍት እና ቤተመጻሕፍት እና አጋዥ ስልጠናዎች የሚያጎለብቱ ኢንቨስትመንቶችን ቅድሚያ መስጠት፤
- በገጠር አካባቢዎች መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መገንባትና ለተማሪዎች (በተለይ ለልጃገረዶች) አዳሪ ትምህርት ቤቶች ጊዜያዊ አማራጮች ላይ ኢንቨስት ማድረግ፤
- የመምህራን ከስራ መልቀቅና መቅረትን ለመቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማበረታቻዎችን በመጠቀም በወረዳ-ደረጃ ትምህርት ቢሮዎች የበለጠ ክትትልን ማረጋገጥ።

አባቶች፣ ወንድሞች፣ የወንድ የዕድሜ እኩዮች፣ እና ባሎች የሴት ልጅ ግርዛትን ጨምሮ ልጃገረዶችንና ሴቶችን የሚጎዳውን የተንሰራፋውን የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ለማስቀጠል ተባባሪ በመሆናቸው፣ የወንድ አመለካከቶችን እና ልምዶችን ለመቀየር ትምህርት ቤቶችንና ማህበረሰብን መሰረት ያደረገ የተሳተፎ ክፍል ጊዜዎች እና የሚዲያ ዘመቻዎች ለመጠቀም የትምህርት ሴክተሩ ከሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሴክተር እና በህፃናት እና ከስርዓተ-ፆታ ላይ ከሚሰሩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ተዋናዮች ጋር መተባበር አለበት። ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

- ሚስቶች እና እህቶች ነጻ የጥናት ጊዜ እንዲያገኙ በተሻለ ሁኔታ እንዴት መደገፍ እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ አባቶች እና ወንድሞችን መርዳት፤
- የሴት ልጅ ግርዛት የተፈፀመባትን ሴት ማግባት ጥሩ እንዳልሆነ፣ ወንዶች እና ወንዶች ልጆች እህቶቻቸውን እና ሴት ልጆቻቸውን እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ እና በሚስታቸው ላይ ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ወንዶችን እና ወንዶች ልጆችን ማስተማር፤
- በማህበረሰቡ ውስጥ የወንዶች ልጆችን ከሴት ልጆች ወሲባዊ ንፅህና እና "የተሳካ" ጋብቻ አመለካከት ለማላቀቅ መስራት፤
- ወንዶችንና ወንዶች ልጆችን ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ሚስት ተግባራዊ ጥቅሞችን (ለምሳሌ የተሻለ ረዳት እንደሆነች፣ በወሊድ ጊዜ የሚደርሱ ጉዳቶች አነስተኛ እንደሚሆኑ) እና ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰችን ልጅ ማግባት የሚያስከትለውን ጉዳት (ለምሳሌ ቶሎ ፍቺ የመከሰት እድል፣ ልጅ የማሳደግ ተግዳሮቶች፣ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አለመጣጣም አደጋ) ማስተማር፤
- የበለጠ ፍትሃዊ የሆነ የቤተሰብ ውሳኔ አሰጣጥ እና የስራ ጫና እንዲኖር ማበረታታት፤ እና ሃይለኛ ወንዶችን መንቀፍ።

ጎሳ እና ባህል የአፋር እና የሶማሌ ማንነት እንዲሁም የሴት ልጅ ግርዛት እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን የማስቀጠል መነሻ በመሆናቸው፣ ልጃገረዶችን እና ሴቶችን የሚጎዱ እምነቶችን እና ልምዶችን ለመቀየር የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሴክተሩ ከትምህርት ሴክተሩ እና ከህፃናት እና ጾታ ተኮር ስራ ከሚሰሩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ከጎሳ መሪዎች ጋር በቅርበት ለመስራት መተባበር አለባቸው። ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

- የሴቶችን ትምህርት ማሳደግ፤
- በራዲዮ፣ በማህበራዊ ሚዲያ፣ በቴሌቪዥን፣ በማህበረሰብ ውይይቶች፣ ትምህርት ቤትን መሰረት ባደረጉ የስርዓተ-ፆታ ክለቦች እና በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የቤት ለቤት ጉብኝትን ጨምሮ ስለ የሴት ልጅ ግርዛት በተለይም ስል ብልት መስፋት ጉዳት በተቀናጀ መልኩ ግንዛቤን ማሳደግ፤
- ያለ ዕድሜ ጋብቻ ጉዳቶችን እና ጋብቻን እስከ ጎልማሳነት ዕድሜ ማዘግየት ያለውን ጥቅም ግንዛቤ ማሳደግ፤
- ማህበረሰቦች - በተለይም ባህላዊ ገራዦች እና እናቶች - ሁሉም አይነት የሴት ልጅ ግርዛት ህገ-ወጥ መሆናቸውን እና በገንዘብ እና በእስራት የሚያስቀጣ መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ።

## መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች

የልጃገረዶችን እና የሴቶችን ህይወት የሚገድበው ሥርዓተ-ፆታ ደንብ ማህበረሰቦችን እና መሪዎችን እነዚህን ደንቦች የማወቅ እና የማስተካከል አቅምን የሚገድቡ በመሆናቸው፣ እምነቶችን እና ልምዶችን ለመቀየር እና የበለጠ ፍትሃዊ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ለማስተዋወቅ ከታዳጊ ወጣቶች እና ጎልማሶች ጋር አብሮ ለመስራት፣ በህፃናት እና በፆታ ላይ ያተኮሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳዮች እና የትምህርት ሴክተሮች ጋር መተባበር በጣም አስፈላጊ ነው።ይህም የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

- ልጃገረዶች ትምህርት እንዲያገኙ እና እንዲሳካላቸው መደገፍ፤
- በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረቱ የልጃገረዶች ክለቦች እና የሥርዓተ-ፆታ ክበቦችን ማጠናከር፤
- አባቶች እና ወንድሞች ሚስቶችን እና እህቶችን ልጃገረዶች የማጥናት ጊዜ እንዲያገኙ እንዴት በተሻለ ሁኔታ መደገፍ እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ መርዳት፤
- አሁን ያሉትን ልምዶች ለመቀየር ወይም በትውልድ መካከል ያለውን ለውጥ ለማበረታታት በሴት ልጅ ግርዛት እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ ዙሪያ በታዳጊነት ዕድሜ ላይ ከሚገኙ ልጃገረዶች እና ወንዶች ልጆች ጋር አብሮ በመስራት፤
- የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን በቀጥታ የሚመለከቱ እና እነዚህ ልጃገረዶች እና ሴቶችን እንዴት እንደሚጎዱ ለእናቶች እና ለአባቶች የወላጅ ትምህርት ኮርሶችን መስጠት፤
- ሴቶች ስለራሳቸውና ሴት ልጆቻቸው መብቶች እንዲያውቁ እና መብቶቻቸውን እንዴት መጎናጸፍ እንደሚችሉ መደገፍ፤
- ወንዶች ጠበኛ የሆኑ የወንድ ባህሪያትን እንዲተዉና የበለጠ ፍትሃዊ የቤተሰብ ውሳኔ እና የስራ ጫና እንዲወስዱ ማበረታታት፤
- በማኅበረሰቡ ውስጥ ወላጆች ከሴት ልጆች ወሲባዊ ንፅህና እና 'የተሳካ' ጋብቻ አመለካከት ለማላቀቅ መስራት
- በማህበረሰቡ ውስጥ እና በማህበራዊ ሚዲያው የለውጥ አርበኞች ሆነው መሥራት የሚችሉ የተማሩ ልጃገረዶችና ሴቶች እና ተራማጅ ወንዶች ልጆችና እና ወንዶችን ያካተተ አርአያ የሆኑ ካድሬዎችን ማቋቋም፤
- ከአካባቢው አመራሮች እና አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በመሆን ስለ አድሎአዊ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ጎጂ ውጤቶች እና የተማሩ እና ኢኮኖሚያዊ አቅም ያላቸው ልጃገረዶች እና ሴቶች በየደረጃው (ግለሰብ፣ ቤተሰብ እና ማህበረሰብ) ያላቸውን ጥቅም ግንዛቤ ማስጨበጥ፤
- ከሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳዮች እና የትምህርት ሴክተሮች ጋር በመተባበር የሃይማኖት እና የጎሳ መሪዎች ስለ ሴት ልጅ ግርዛት እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ ጎጂ ውጤቶች ማስተማር።

## የግብርና፣ ስራ እና አደጋ ስጋት አመራር ሴክተሮች

ዓለም አቀፍ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ያለ ዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል ከሁሉ የተሻለው መንገድ ልጃገረዶችን በተቻለ መጠን ለረጅም ጊዜ በትምህርት ቤት ማቆየት በመሆኑ፣ የማህበራዊ ጥበቃን በመጠቀም ልጃገረዶችን እንዲያስተምሩና ጋብቻን እንዲያዘገዩ ቤተሰቦችን ለማበረታታት የግብርናው ዘርፍ እና የአደጋ ስጋት አስተዳደር እና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ከትምህርት ሴክተሩ ጋር ሊተባበሩ ይገባል። ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

- ልጃገረዶች ወደ ቤታቸው ይዘውት የሚሄዱ ከተጨማሪ ምግብ ጋር የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም መጀመር/ ማስቀጠል፤
- የሴቶችን ትምህርት ለመደገፍ በጥሬ ገንዘብ እና በንብረት ዝውውሮች ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ፤ ይህም ቀጣይነት ባለው ያለ ዕድሜ ጋብቻ ሁኔታና በወላጆች እና ታዳጊዎች በጾታ ላይ ያተኮረ ፕሮግራም ውስጥ ባላቸው ተሳትፎ መሰረት፤ እና የምርታማ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ተግባራዊ በሚሆንበት ሁኔታ ላይ በመመስረት ይሆናል።

በአርብቶ አደር ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉ ልጃገረዶች እና ሴቶች የራሳቸውን ገቢ የማስፋት እድሎች በጣም ውስን በመሆናቸው፣ ከያለ ዕድሜ ጋብቻ ሌላ አማራጭ እንዲሰጣቸው እና በማህበረሰቡ ውስጥ ትልቅ ቦታ እንዲኖራቸው አማራጭ መንገድ እንዲሰጣቸው ለማድረግ የግብርና እና የስራ ሴክተሮች የሴቶችን የመተዳደሪያ አማራጮችን ለማስፋፋት ጥረቶችን ማሳደግ አለበት። የልጃገረዶች እና የሴቶችን የተሻሻለ የፋይናንስ ተደራሽነት የሴት ልጅ ግርዛትን የበለጠ እንዳያስተጓጉል ከግንዛቤ ማስጨበጫ ጋር ሊጣመሩ ይገባል። ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

- ለትላልቅ ልጃገረዶች እና ሴቶች የእንስሳት እርባታ፣ የሰብል እርሻ፣ የንግድና ሌሎች በባህላዊ ተቀባይነት ያላቸው የሙያ ክህሎቶች, ህይወት ክህሎቶችንና የገንዘብ / የንግድ ክህሎቶችን ያካተተ የስልጠና ኮርሶችንማዘጋጀት፤
- ትላልቅ ልጃገረዶች እና ሴቶች የመደበኛ ቁጠባ እና ብድር እድሎች እንዲኖሯቸው ወጣት ልጃገረዶችን ለማነሳሳት እና ባህላዊ የሥርዓተ-ፆታ ሚናዎችን ለመቃወም

ውጤታማ የግብርና ሥራ ፈጣሪዎች የሆኑ ሴቶችን (ለምሳሌ በወተት እርባታ፣ በንብ እርባታ ወይም በዶሮ እርባታ) በማሳያነት በሬዲዮ ፕሮግራሞች እና በአገር ውስጥ ትዕይንቶች ማቅረብ።

## የጤና ሴክተር

የሴት ልጅ ግርዛት የተፈፀመባቸው ልጃገረዶች እና ሴቶች ለእድሜ ልክ ህመም እና በሽታ የሚጋለጡ በመሆናቸው፣ የሴት ልጅ ግርዛት በህክምና ድጋፍ እየጨመረ በመምጣቱ፣ እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ እና የታዳጊዎች እርግዝናን ማለያየት የሚቻል በመሆኑ፣ የጤና ቢሮዎች በክልልና በወረዳ ደረጃ ያሉ የጤና ባለሙያዎች ጎጂ ልማዶችን በመቀነስ ረገድ የድርሻቸውን እንዲወጡ ጥረታቸውን አጠናክረው መቀጠል አለባቸው።

ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን እና ሌሎች የጤና እንክብካቤ ሰጭዎችን ስለ ሴት ልጅ ግርዛት አካላዊና ስነ-ልቦናዊ ጉዳቶች ማሰልጠን፤
- የማህበረሰቡ አባላትን ማስተማር - (በቅድመ ወሊድ እና የህፃናት ክትባት ወቀት እና የአካባቢ እምነትን እና ልማዶችን ከግምት ውስጥ ማስገባትን ጨምሮ) ስለ ልዩ ልዩ የሴት ልጅ ግርዛት ዓይነቶች (የትኞቹ ድርጊቶች ሱና በሚለው አገላለጽ ስር ሊካተቱ የማይችሉትን ጨምሮ) እና የሴት ልጅ ግርዛት የሕይወት ዘመን ጉዳቶች ማስተማር፤
- የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን በመመልመል እየተቀየሩ ያሉ ልማዶችን እንዲከታተሉ ማድረግና የመልእክት ማስተላለፊያ እና ፕሮግራሚንግ ስራዎች በተሻለ ሁኔታ እንዲተገበሩ ለሁለቱም የጤና ቢሮዎች እና የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊዎች በመደበኛነት ማሳወቅ፣
- የተገረዙ ልጃገረዶች እና ሴቶች በተለያዩ የሕይወታቸው ደረጃዎች ተገቢውን የጤና እንክብካቤ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ።
- የጤና ባለሙያዎች የቤተሰብ ህጉ በሴት ልጅ ግርዛት ላይ የጣለውን እገዳ ማወቃቸውን እንዲያረጋግጡ ማሰልጠን፣ በ2017ቱ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር መመሪያ መሰረት ይህን ተግባር ሲፈጽም የተገኘ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ላይ ቅጣቶችን ማስፈጸም፤ ይህም ከክልል ጤና ጥበቃ ቢሮዎች እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ ስለ ቤተሰብ ህግ በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ስላለው እገዳ ማወቃቸውን እንዲያረጋግጡ ስልጠና መስጠትንና ግልጽ መመሪያን ማካተት አለበት።
- ፍላጎቱ ዝቅተኛ በሆነባቸው አካባቢዎች እንኳን ቢሆን ያገቡ ልጃገረዶች አካላቸው ዝግጁ እስኪሆን ድረስ የእርግዝና መከላከያ እንዲጠቀሙ እንዲያስተምሩ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎችን መደገፍ፤
- የተባበሩት መንግስታት የህጻናት መርጃ ድርጅት (ዩኒሴፍ) እና የተባበሩት መንግስታት የስነ ህዝብ ፈንድ ካቋቋሙት እና የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አካል ከሆነው የምስራቅ አፍሪካ መድረክ ጋር በመሆን የሴት ልጅ ግርዛትን ለመቅረፍ ከድንበር ተሻጋሪ ትብብርን ጨምሮ ስልታዊ እርምጃዎችን ለማሳወቅ በተቋቋሙ አመታዊ ስብሰባዎች ላይ መሳተፍና ማስረጃዎችን ማጋራት።

## የክልል መንግስታት

የአፋር እና ሶማሌ ክልሎች የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን በመቀነስ ረገድ ሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች ያሳዩትን እድገት እስካሁን እያረጋገጡ ባለመሆናቸው፣ የክልል መንግስታት መሪዎች የልጃገረዶችን እና የሴቶችን ህይወት የሚያሻሽል ማህበራዊ ለውጥን እንዲሁም ሰፊ የልማት ውጤቶችን በማሳደግ ላይ ኢንቨስት ማድረግ አለባቸው። ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት።

- ለውጥን ለማበረታታት ፈቃደኛ የሆኑ (በተለይም የጎሳ እና የሀይማኖት መሪዎች፣ ባህላዊ ገራዦችና፣ በሴት ልጅ ግርዛት ወይም ያለ ዕድሜ ጋብቻ ምክንያት የራሳቸው ወይም የሴት ልጆቻቸው ህይወት የተጎዳባቸው ሴቶች) ሻምፒዮናዎችን ለመለየት ጥረት ማድረግ፣
- ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን የሚከለክለውን ብሔራዊ የቤተሰብ ህጉን ማጽደቅ፤
- ልጃገረዶች እና ሴቶች መብቶቻቸውን እንዳያስጠብቁ የሚከለክሉትን የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን እና ተግባራትን ለመግታት በቂ የሰው እና የገንዘብ ሀብት መመደብ፤
- በሴክተር ደረጃ ያሉ ተዋናዮች ከሴት ልጅ ግርዛት እና ያለ ዕድሜ ጋብቻ ጋር በተያያዘ የተሰጣቸውን ግዴታ እየተወጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ለመግታት የተነደፉ ፕሮግራሞችን፣ ስርጭቱ ከፍተኛ በሆነባቸው ራቅ ባሉ ማህበረሰቦች ላይ በማተኮር፣ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ክትትል እና ግምገማ ላይ ኢንቨስት ማድረግ።

## የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን የማስቆም ብሄራዊ ጥምረት

የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን የማስቆም ብሄራዊ ጥምረት በልዩ ሁኔታ ድርጊቱን ለማስወገድ ጥረቶችን ለማስቀጠልና ለማፋጠን እየሰራ በመሆኑ፣ የጥምረቱ አባላት በጋራ አዳዲስ የለውጥ መንገዶችን መቀየስ እና አዳዲስ የለውጥ ኃይሎችን በመለየት በየደረጃው ያለውን የማጥፋት ጥረቶችን መደገፍ አስፈላጊ ነው። ህብረቱ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:

- የብሔራዊ እና የክልል ህጎችን ለማስማማት ከክልል ባለስልጣናት ጋር መስራት፤ ግንዛቤን ለማሳደግ እና አፈፃፀምን ለማሻሻል ከክልል በታች ካሉ ባለስልጣናት ጋር መስራት፤ ልምዶቹን ለማስወገድ ቁርጠኝነትን ለማጠናከርና በቀበሌ ደረጃ ድጋፍ ለማድረግ ከአካባቢው ባለስልጣናት ጋር መስራት፤ እና የተቀናጁ እና የሚተገበሩ እቅዶችን ለማዘጋጀት ከሀይማኖት እና የጎሳ መሪዎች ጋር በመስራት፤
- ሴት ልጆችን በትምህርት ቤት ለማቆየት የሚደረገውን ጥረት ማጠናከር፣ የሴቶች ክለቦችን እና የሥርዓተ ጾታ ክበባትን ማስፋፋት እና የሴት ልጅ ግርዛትን በህክምና መዋጋትን ጨምሮ ከሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች (በተለይ ከጤና፣ ከትምህርት እና ፍትህ) ጋር በጋራ በመስራት ያለ ዕድሜ ጋብቻን እና የሴት ልጅ ግርዛትን ለመከላከል በመንግስት የዘርፍ እቅዶች ውስጥ ማካተት፤
- በታዳጊነት ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጃገረዶች እና አሳዳጊዎቻቸው አድሏዊ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ለመተው

እና አቅም ያለው እና ገለልተኛ ህይወትን ለመምራት ያላቸውን አቅም ለማሳወቅ እና ለማነሳሳት ለጋዜጠኞች እና የሚዲያ አዘጋጆች ስለ ልጃገረዶች እና ሴቶች አቅም እንዲዘግቡ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ፤
- ማስረጃን በማመንጨት እና በማስረጃ የተደገፈ ድጋፍ እና ትምህርት በመስጠት ላይ ኢንቨስት ማድረጉን መቀጠል፡፡

## ረጂዎች

የሴት ልጅ ግርዛትን እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ማስቀረትብዙ ሀብት የሚጠይየሚጠይቅ እና የማያቋርጥ የረጅም ጊዜ የመፍትሄ እርምጃን የሚጠይቅ በመሆኑ፣ የልማት አጋሮች በማስረጃ የተደገፈ ፕሮግራሚንግ ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ እና ማሳደግ አለባቸው፡፡ ይህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡፡

- ራቅ ያለ ቦታ የሚገኙ አርብቶ አደር ማህበረሰቦች ጨምሮ ትምህርት ለሁሉም ልጆች ለማድረስ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ትምህርት ቤቶችን መገንባት ብቻ ሳይሆን ዘላቂ ውጤት ሊያመጣ የሚችል የመምህራንን ስልጠና እና የትምህርት ቤት ምገባን መደገፍ፤
- የልጃገረዶችን ትምህርት ለማሻሻል (እና ያለ ዕድሜ ጋብቻን ለመቀነስ) በጣም ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች ማህበራዊ ጥበቃን ማስፋፋት፤
- የአካባቢያዊ አገልግሎቶችን ለማሻሻል ክልላዊ አቅምን ማጠናከር፤
- ገዳቢ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ለመቀየር በፕሮግራም ላይ ኢንቨስት ማድረግ፤
- የአውድ ልዩነትን ከፍ ለማድረግ ፕሮግራሞችን ማሻሻል እና ማስተካከል፤
- በጠንካራና ዘላቂ ክትትል፣ ግምገማ እና ምርምር ላይ ኢንቨስት በማድረግ ለውጥን ለመከታተል እና ውስን ሀብቶችን ከአውድ ልዩነት አንፃር እንዴት በተሻለ ሁኔታ መመደብ እንደሚቻል እና እንዲሁም ውጤታማ የፕሮግራም አወጣጥን እንዴት ከፍ ማድረግ እንደሚቻል ማሳወቅ፡፡

## ማጣቀሻዎች


28toomany and Orchid Project (2023) FGM/C in Ethiopia: coun- try profile update June 2023 (https:// www.fgmcri.org/media/uploads/Country%20Research%20and%20Resources/Ethiopia/ethiopia_country_profile_update_v2_(august_2023).pdf)

Central Statistical Agency of Ethiopia (CSA) and ICF (2017) Ethiopia Demographic and Health Survey 2016. Addis Ababa, Ethiopia, and Rockville, Maryland, USA: CSA and ICF (https://dhsprogram.com/pubs/pdf/FR328/FR328.pdf)

Elezaj, E., Ramful, N., Cebotari, V. and De Neubourg, C. (2019) Gender equality, women's empowerment and child wellbeing in Ethiopia. UNICEF Ethiopia and Ministry of Women, Chil- dren and Youth (www.unicef.org/ethiopia/media/2811/file/Gender%20Equality,%20Women's%20empowerment%20and%20child%20wellbeing%20in%20Ethiopia.pdf)

Endale, K., Jones, N., Presler-Marshall, E., Woldehanna, T., Ya- dete, W., Abdisalam, A., Alemu, A., Gebeyehu, Y., Gezahegne, K., Murha, R., Neumeister, E., Tesfaye, A., Tilahun, K. and Work- neh, F. (2022) Exploring the patterning and drivers of FGM/C and child marriage in pastoralist Ethiopia. Baseline report from Afar and Somali regions. London: Gender and Ado-lescence: Global Evidence (www.gage.odi.org/publication/exploring-the-patterning-and-drivers-of-fgm-c-and-child- marriage-in-pastoralist-ethiopia-baseline-report-from-afar- and-somali-regions)

Endale, K., Presler-Marshall, E., Yadete, W., Jones, N., Gebeyehu, Y., Abdiselam, A., Tilahun, K., Workneh, F. and Woldehanna, T. (2025) FGM and child marriage attitudes, norms and prac- tices: Midline findings. Report. London: Gender and Ado-les- cence: Global Evidence. (xxx)

Erulkar, A. (2022) 'Changes in the prevalence of child marriage in Ethiopia, 2005–2016'. Reproductive Health 19(Suppl 1): 195 (https://doi.org/10.1186/s12978-021-01234-4)

Islamic Relief Worldwide (2018) One cut too many: Islamic Relief policy brief on female genital mutilation/cutting. Birmingham: Islamic Relief Worldwide (www.islamic-relief.org/wp-content/ uploads/2018/03/FGM-CSW62.pdf)

UNICEF (2023) 'Is an end to child marriage within reach? Latest trends and future prospects'. UNICEF Data, 5 May (https:// data.unicef.org/resources/is-an-end-to-child-marriage-with- in-reach)



ይህ የፖሊሲ አጭር መግለጫ የስርዓተ ጾታ እና ታዳጊነት፡ ዓለም አቀፍ ማስረጃ (ጌጅ) ፕሮግራም ውጤት ሲሆን ይህም ከእንግሊዝ መንግሥት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ በአይሪሽ እርዳታ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ የተገለጹት አመለካከቶች እና በውስጡ የተካተቱት መረጃዎች የዩኬን መንግስት ወይም የአየርላንድ መንግስትን ይፋዊ ፖሊሲዎች የሚያንፀባርቁ አይደሉም፤ በዩኬ መንግስት ወይም በአየርላንድ መንግስትም አልተደገፉም፡፡ ለእንደዚህ አይነት ወይም ከዚያ ጋር የተያያዘ ማንኛውም አይነት አመለካከት ወይም መረጃ ሃላፊነት አይወስድም፡፡

ISBN: 978-1-915783-90-5


GENDER & ADOLESCENCE: GLOBAL EVIDENCE

Ambasáid na hÉireann
Embassy of Ireland

UKaid from the British people